# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 141 ጥር 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የድንጋይ ከሰል ማጣሪያ ፋብሪካ በቅርቡ ሥራ ይጀምራል

## - 150 ቶን ከሰል በሰዓት የማምረት አቅም አለው
## - የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን 75 በመቶ የድንጋይ ከሰል ፍላጎት ያሟላል

**ውብሸት ሰንደቁ**

ታርጫ፡- በዳውሮ ዞን ታርጫ ከተማ በ5 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር እየተገነባ የሚገኘው የድንጋይ ከሰል ማምረቻ ፋብሪካ ከሁለት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሥራ እንደሚጀምር ተገለጸ፡፡

የጋሞ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዳዊት ገበየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ ከፍተኛ የማዕድን ክምችት አለ፡፡ በተለይ የከሰል ማዕድን ክምችት በከፍተኛ መጠን ይገኛል፡፡

ይህንን የከሰል ማዕድን አልምቶ ሀገርን እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ መጥቀም ያስፈልጋል ያሉት ዋና አስተዳዳሪው፤ ፋብሪካው በ5 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ካፒታል እየተገነባ የሚገኝ መሆኑን ተናግረዋል፡፡


**በኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# "የጋራ ተጠቃሚነትን መርሕ ያደረገውን ስምምነት ሳይረዱ ኢትዮጵያን ማውገዝ ተቀባይነት አይኖረውም"

- ፍጹም አረጋ
በካናዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አባባ፡- የባሕር በር ስምምነት የጋራ ተጠቀሚነትን መርሕን መሠረት ያደረገ መሆኑን ሳይረዱ ኢትዮጵያን ያወገዙ አካላትና ሀገራት ተቀባይነት የላቸውም ሲሉ በካናዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር ፍጹም አረጋ ገለጹ፡፡

በካናዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር ፍጹም አረጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚነቷን ለማሳደግ ስትሠራ ጥቂት ሀገራት ለመቃወም ይሞክራሉ፡፡

የኢትዮጵያና ሶማሌላንድ የባሕር በር ስምምነት የጋራ ተጠቃሚነትን መርሕ ያደረገ መሆኑን ባለመረዳት አንዳንድ ሀገራት እየተቃወሙ ይገኛል ያሉት አምባሳደር ፍጹም፤ ተቃውሟቸው ጥቅማችን ይነካብናል በሚልና በአካባቢው የበላይ ሆኖ ለመታየት ከመፈለግ የመነጨ


**"የጋራ ተጠቃሚነትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**







አቶ ኤልያስ ከድር

# በክልሉ በመጪው ክረምት 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ታቅዷል

## -እስካሁን 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በ2016 ዓ.ም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል መታቀዱን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ እስካሁን 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል፡፡


**በክልሉ በመጪው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# በክልሉ በዘንድሮው የምርት ዘመን ከ82 ሺህ ቶን በላይ የቡና እሸት ተሰብስቧል

-67 ሺህ ቶን የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል


ገጽ 4










ዶ/ር ዓለምፀሐይ ጌታቸው

# የሥጋ ደዌ ስርጭት በከፍተኛ መጠን መቀነሱ ተነገረ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የሥጋ ደዌ በሽታ ስርጭት ቀደም ካሉ ጊዜያት አንጻር በከፍተኛ መጠን መቀነስ መቻሉ ተገለጸ። በሽታውን ሙሉ በሙሉ ከሀገራችን ለማጥፋት አሁንም ቀሪ የቤት ሥራዎች መኖራቸው ተጠቁሟል።

በአለርት ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቆዳና የአባላዘር ስፔሻሊስት ሕክምና በሆስፒታሉ የቆዳና የአባላዘር ሕክምና ክፍል ኃላፊ ዶ/ር ዓለምፀሐይ ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፣ ቀደም ሲል ከ10ሺ ሰዎች መካከል 19ነጥብ8 ያህሉ በበሽታው ይያዙ የነበረ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ በ2022 በወጣው መረጃ መሠረት ይህንን ቁጥር ወደ 0ነጥብ 32 ማውረድ ተችሏል።

የበሽታውን ስርጭት በዚህ መጠን ለመቀነስ እ.ኤ.አ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ለበሽታው ተጠቂዎች ጭምር መድኃኒት መሰጠት መጀመሩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል ብለዋል።

ስርጭቱን በከፍተኛ መጠን መቀነስ ቢቻልም፣ ዛሬም በመላው የሀገሪቱ ክፍል 2558 አዲስ የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች መገኘታቸው እ.ኤ.አ በ2022 የወጣው መረጃ አመላክቷል።

አዲስ ከተገኙት የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች መካከል 7ነጥብ2 ከመቶ ያህሉ ሕጻናት ናቸው። ይህም ዛሬም በሽታው በማኅበረሰቡ ውስጥ እየተላለፈ መሆኑን አመላካች ነው።

በሽታውን ሙሉ በሙሉ ከሀገራችን ለማጥፋት አሁንም ሰፊ ሥራ ይጠይቃል ያሉት ዶ/ር ዓለምፀሐይ፣ በሀገራችን መጠኑ ይለያይ እንጂ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች የበሽታው ስርጭት አለ። የበሽታው ስርጭት ያለባቸው 93 ያህል ወረዳዎችም ተለይው የግንዛቤ ማስጨበጫና የሕክምና አገልግሎቶች በመስጠት ላይ ናቸው።

ቀደም ባሉ ጊዜያት በኅብረተሰቡ ዘንድ የሥጋ ደዌን በዘር የሚተላለፍ በሽታ አድርጎ የመቁጠር የተሳሳተ ግንዛቤ እንደነበር ያነሱት ዶ/ር ዓለምፀሐይ፣ ከበፊቱ አንጻር አሁን ላይ ኅብረተሰቡ ስለ በሽታው የነበረው አመለካከት እየተቀየረ እንደመጣ ገልጸዋል።

የተሳሳተ አመለካከት ከመኖሩ የተነሳ የበሽታው ተጠቂዎች ይደርስባቸው የነበረው መገለልና መድልዎም ቀንሷል ይላሉ።

አመለካከቱ እየተቀየረ ቢሆንም፣ ዛሬም መገለልን በመፍራት ቤታቸው የተቀመጡ ብዙ ታካሚዎች መኖራቸውን ግን ዶ/ር ዓለምፀሐይ ጠቁመዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ የሥጋ ደዌ ስርጭትን ሙሉ በሙሉ ከሀገር ለማጥፋት በሚደረገው ጥረት ጤና ሚኒስቴር ከሌሎች አጋር አካላትና ሥጋ ደዌ ላይ ከሚሠሩ ሆስፒታሎች ጋር በመሆን ለተለያዩ የጤና ባለሙያዎች በየጊዜው ሥልጠናዎች በመስጠት ላይ ይገኛል። የሥጋ ደዌ ይበዛባቸዋል የሚባሉ አካባቢዎችን በመለየትም በዘመቻ መልኩ የሕክምናና የግንዛቤ ማስጨበጫ አገልግሎቶችን እየሰጠ ነው።

# በመዲናዋ የቱሪዝም ዘርፍ ከ55 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር በላይ ወደኢኮኖሚው ፈሰስ ሆኗል

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት ከመዲናዋ የቱሪዝም ዘርፍ ከ55 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው ፈሰስ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፋት ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን ዓይናቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት በቱሪዝሙ ዘርፍ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ቱሪስቶች በተለያዩ መንገዶች ከ55 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ሆኗል።

በስድስት ወራቱ አፈጻጸም ከዕቅድ አንጻር ከፍተኛ ሥራ መከናወኑን ጠቅሰው፤ ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ቱሪስት ለመሳብ ታቅዶ ከአራት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ወደ ከተማዋ መጥተዋል ያሉት አቶ ሳምሶን፤ ከዕቅዱ አንጻር 58 በመቶ ጭማሪ ማሳየቱን ጠቁመዋል።

ከሀገር ውስጥ ቱሪስቶች 25 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ መሆኑን ዳይሬክተሩ አመላክተዋል።

በተጨማሪ 465 ሺህ 366 የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች ወደ ከተማዋ መምጣታቸውን አመልክተው፤ ከውጭ ሀገራት ቱሪስቶች 29 ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ፈሰስ ሆኗል ብለዋል።

ከቱሪዝም ዘርፉ በአብዛኛው ለመንግሥት በቀጥታ ከሚገባ ገንዘብ ይልቅ፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች ፈሰስ የሚደረገው ገንዘብ ይልቃል ሲሉ አስረድተዋል።

ከቱሪስቶች ለሙዚየም ጉብኝት ክፍያ፣ ለፓርኮች ጉብኝት፣ ለሆቴል አገልግሎት፣ ለምግብ፣ ለትራንስፖርት፣ ለስጦታና ማስታወሻ ዕቃዎች ግዢና ለተለያዩ በሚገኝ ገንዘብ ኢኮኖሚውን ማጠናከር የሚቻልበት ፈሰስ መገኘቱንም ተናግረዋል።

ወደ ከተማዋ የመጡ የሀገር ውስጥና ውጭ እንግዶች ለተለያዩ የቱሪዝም ዓላማዎች የመጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በተለያዩ ሁነቶች ለመሳተፍ፣ ለኢሬቻና ለሃይማኖታዊ በዓላት፣ ለጉብኝት፣ ለዘመድ ጥየቃ፣ ለሕክምና አገልግሎት፣ ለስፖርታዊ ውድድሮችና ለተለያዩ ጉዳዮች መምጣታቸውን አስረድተዋል።

የቱሪዝም ዘርፉ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ገቢ ማደግና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን በመግለጽ፤ ባለፉት ስድስት ወራት በቱሪዝም ዘርፉ ከሰባት ሺህ በላይ ወጣቶችና ሴቶች በቋሚና ጊዜዊነት የሥራ ዕድል ተጠቃሚ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በቀሪ ስድስት ወራት ውስጥ እንደ ከተማ ያሉ የቱሪዝም መስሕብና መዳረሻዎችን ለጎብኚዎች ምቹ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራና በተለይም ቱሪዝምን ማዕከል ያደረጉ የሥራ ዕድል ፈጠራዎች እንደሚከናወኑ አመላክተዋል።

በተጨማሪም የከተማዋን የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስት ቁጥር ለማሳደግ የተለያዩ ሁነቶች የሚዘጋጁ መሆኑን ጠቅሰው፤ በከተማው ውስጥ ያሉ የቱሪስት መስሕብ ቦታዎችን በዓለም አቀፍ መድረኮች የማስተዋወቅና ተደራሽነታቸውን የማድረግ ሥራ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

# በመዲናዋ 19 ጤና ጣቢያዎች በቀዶ ጥገና የማዋለድ አገልግሎት እየሰጡ ነው

**መዓዛ ማሞ**



ፎቶ፡ ገበበ ገብሬ

አዲስ አበባ፡ በመዲናዋ 19 ጤና ጣቢያዎች በቀዶ ጥገና ጥራቱን የጠበቀ የማዋለድ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

በጥር ወር የሚከበረው የጤናማ እናትነት ወር "ፍትሐዊነት፣ ተደራሽነት እና ጥራት ያለውን የቅድመ ወሊድ ክትትል በወቅቱ በማስጀመር ጤናማ እናትነትን እናረጋግጥ" በሚል መሪ ሀሳብ በአዲስ አበባ ደረጃ በዘውዲቱ ሆስፒታል በተለያዩ ዝግጅቶች ለ10ኛ ጊዜ ትናንት ተከብሯል ።

በፕሮግራሙ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ ወይዘሮ ሀንጋቱ መሐመድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ለእናቶች ሞት ምክንያት ናቸው ያላቸውን ችግሮች በመለየት የተግባር ስልትና አዳዲስ አሠራሮችን በመንደፍ ላይ መሆኑን ተናግረዋል። በዚህም በመዲናዋ 19 ጤና ጣቢያዎች ጥራቱን የጠበቀ በቀዶ ሕክምና የማዋለድ አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በጤና ተቋማት የእናቶች ማቆያ ማስፋፊያ ሥራን በማጠናከር በደም መፍሰስ ምክንያት የሚከሰተውን የእናቶች ሞት ለመቀነስ እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ የጤና ባለሙያዎች ክህሎት ላይም የማሻሻል ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

ጥራት ያለው የቅድመ ወሊድ ክትትል በወቅቱ ማስጀመር እናቶች በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድና ከወሊድ በኋላ ለሕመምና ሞት የሚያበቋቸውን መንስኤዎች በጊዜው አውቆ ለመከላከል እንደሚያግዝ ተናግረው፤ የጤናማ እናትነት ወሩ በዚህ ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ በተለያየ መርሐ ግብር እንደሚከበር ተናግረዋል።

መንግሥት የእናቶችን ጤና አገልግሎትን በነፃ እንዲሰጥ ከማድረግ ባሻገር አገልግሎቱን ለማዘመን፣ በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ እና አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የእናቶችን ጤና መጠበቅ ሀገርን መጠበቅ ነው ያሉት ወይዘሮ ሀንጋቱ፤ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የባለድርሻ አካላት እና መላው ኅብረተሰብ ከጤና ሴክተር ጋር በቅንጅት በመሥራት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።

በመርሐ ግብሩ የተገኙት በጤና ሚኒስቴር የእናቶች ጤና አስተባባሪ ሲስተር ዘምዘም መሐመድ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ እንደ ጤና ሚኒስቴር የእናቶችን የቅድመ ወሊድ ክትትል ጊዜ በመጨመር እና ሁሉም እናቶች በጤና ተቋም እንዲወልዱ በማድረግ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ እየተሠራ ነው።

የእናትነት ወሩ እንደ ሀገር ለ18ኛ ጊዜ እንደሚከበር አስታውሰው፤ ሁሉም ኅብረተሰብ የእናቶችን ሞት ለመቀነስ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት አለበት ብለዋል።

በመርሐ ግብሩ የጤና ሚኒስቴር ተወካዮች፣ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊዎች እና የጤና ባለሙያዎች ተገኝተዋል።

# በባቱ ከተማ ከ17 ሺህ በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ባቱ፡- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ባቱ ከተማ በ2016 የትምህርት ዘመን ከ17 ሺህ በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ መሆናቸውን የባቱ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ አሕመዲን እስማኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የትምህርት ቤት ምገባ ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት አቀባበልና ውጤት እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። የተማሪዎችን ለረሃብ ተጋላጭነት በማስቀረት የተሟላ ጤናና የአመጋገብ ሥርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

የሀገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራሙ በተለይም በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግር ምክንያት የተጎዱ ተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙና በትምህርታቸውም ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዝ ነው ያሉት ከንቲባ አሕመዲን፤ በባቱ ከተማ በ2016 የትምህርት ዘመን ከ17 ሺህ በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ፕሮግራሙ የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነትን ከማሻሻል ጎን ለጎን ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ያሉት ከንቲባ አሕመዲን፤ ፕሮግራሙ ለቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በየዕለቱ በንጥረ ነገር የበለፀገ ምግብ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ የተሻለ ትውልድ ለማፍራት ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታል ብለዋል።

እንደ ከንቲባ አሕመዲን ገለፃ፤ በ2 ወር ብቻ ማለትም በኅዳርና በታኅሳስ ወር ከ126 ሚሊዮን ብር በላይ በሰው ተኮር ሥራዎች ላይ ወጪ ተደርጓል። ይህም በከተማ ከሚገኙ ባለሃብቶችንና ለጋስ ድርጅቶች የተሰበሰበ ነው። በዚህም ከተማ አስተዳደሩ ለአቅመ ደካሞች ከ65 ቤቶች በላይ በመገንባት አስረክቧል። ከዚህም ባለፈ ከ10 ሺህ 345 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ አስረክቧል።

ፕሮግራሙ በተለያየ ችግር ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱና ሌሎችም ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ከማድረግና ፍትሐዊነትን ከማረጋገጥ አንፃር ወሳኝ ነው። ፕሮግራሙ በከተማው የተሳካ እንዲሆንና ቀጣይነት እንዲኖረው የክልሉ መንግሥት የሚቻለውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጿል ነው ያሉት ከንቲባ አሕመዲን።

ከንቲባ አሕመዲን አክለውም፤ የትምህርት ንቅናቄ ሥራዎችን ማስቀጠል፤ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች በካላንደሩ መሠረት ትምህርት ማስጀመር፤ ቀሪ መጽሐፍትን ማሳተም እና ለነባር መምህራን የጽሑፍ ምዘና መስጠት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ አብራርተዋል።

በተጨማሪም የዝግጅት ሥራዎችን ማጠናቀቅ፣ ነባር ግንባታዎችን ማጠናቀቅ እንዲሁም ትምህርት ልማት አጋሮችን ተሳትፎ ማበረታታት ከተማው በ2016 የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት ናቸው። የምገባ ፕሮግራሙም የትምህርት ቤቶችን ውስጣዊ ብቃትና የተማሪዎችን ተሳትፎን የሚያሳድግ በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

# ሆስፒታሉ የመካንነት የምርመራ አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ነው

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**



አዲስ አበባ፡- አበበች ጎበና የእናቶችና ሕጻናት ሆስፒታል የመካንነት የምርመራ አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ነው።

የሆስፒታሉ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አናኒያ ሰሎሞን ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ሆስፒታሉ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችለውን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ሆስፒታሉ ለእናቶችና ሕጻናት የተሻለ የጤና አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ ግንባታው ተጠናቆለት ወደ አገልግሎት የገባው ከሁለት ዓመታት በፊት ሲሆን፣ በሁለት ዓመት ከአራት ወራት ውስጥ 23ሺ 400 እናቶችን አዋልዷል።

እናቶችን ከማዋለድና ከማኅፀንና ፅንስ ሕክምና መሠረታዊ አገልግሎት በተጨማሪ የላቀ የጨቅላ ሕጻናት የሕክምና አገልግሎት፣ የሽንት ቱቦ ምርመራ፣ የቅድመ ካንሰር ምርመራና ለሴቶችና እናቶች የግንዛቤ ማስጨበጫዎችም በሆስፒታሉ ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ይገኙበታል።

ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሆስፒታሉን አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ታካሚዎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን የጠቆሙት ዶ/ር አናኒያ፣ ከጤና አገልግሎቱ ባሻገር ሆስፒታሉ እንደ ሜዲካል ቱሪዝም የምንገለገልበትም ጭምር ነው ብለዋል። በሆስፒታሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራትና ስፋት ለመጨመር በየጊዜው እየሠራ እንዳለና በአጭር ጊዜ ውስጥም ለውጥ ማምጣት እንደቻለም ገልጸዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት ሆስፒታሉ ለእናቶችና ሕጻናት የሚሰጠውን አገልግሎት በማላቅ በቅርቡ ደግሞ የመካንነት ምርመራ መስጠት የሚጀምር ይሆናል። ሆስፒታሉ የመካንነት የምርመራ አገልግሎት መስጠት ይቻለው ዘንድ አስፈላጊ የሆኑ የመሣሪያ ግዢ እየተካሄደ ሲሆን ሌሎች ግብዓቶችንም በማሟላት ሂደት ላይ ነው። ለአገልግሎቱ መጀመር የጤና ሚኒስቴርን ጨምሮ ሌሎችም አካላት ጥረትና ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ።

በመካንነት ምርመራ፣ የመካንነት ችግር ካለባቸው 100 ሴቶች መካከል 40 ከመቶውን የልጅ እናት የማድረግ እድል እንዳለ የጠቆሙት ዶ/ር አናኒያ የአገልግሎቱ መጀመር ለብዙ እናቶች ልጅ የማቀፍ ሕልም እውን መሆን አስተዋፅዖ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

የአበበች ጎበና ሆስፒታል የመካንነት ምርመራ ሲጀምር፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ቀጥሎ ሁለተኛው የመካንነት ምርመራ አገልግሎት የሚሰጥ የሕዝብ ሆስፒታል ይሆናል። ቀደም ሲል የመካንነት የጤና አገልግሎት ለማግኘት ረጅም ቀጠሮ ሲጠብቁ ለነበሩ የአገልግሎቱ ፈላጊዎች የተሻለ መፍትሔ ይሆናል ተብሎም ይጠበቃል።

# በመዲናዋ ደምብ በጣሱ ከ529ሺህ በላይ አሽከርካሪዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በግማሽ ዓመቱ ከ529ሺ በላይ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ በመጣሳቸው ርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አማረ ታረቀኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የትራፊክ ደንብ ማክበር የአደጋ መንስኤዎችን በመቀነስ በሰው ሕይወት ብሎም በንብረት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል ያግዛል። በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት በአሽከርካሪዎች ላይ በተደረገ የቁጥጥር ሥራም ከ529ሺህ በላይ አሽከርካሪዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል።

በአዲስ አበባ ከተማ ከ700ሺ በላይ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን የገለጹት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ የተነሳም የተለያዩ አደጋዎች እንደሚደርሱ ገልጸዋል።

አቶ አማረ ባለሥልጣኑ ባደረገው ቁጥጥር ከሐምሌ 1 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ529ሺ በላይ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ ተላልፈው በመገኘታቸው ርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል።

ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ማሽከርከር ለአሽከርካሪ፣ ለተሳፋሪ ብሎም ለእግረኛ ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ገልጸው፤ የቅጣቱ ዓላማ አሽከርካሪን መቅጣት ሳይሆን አደጋን መቀነስ ያለመ መሆኑ ጠቅሰዋል።

ባለሥልጣኑ የትራፊክ ሕጎችን ከማስከበር በተጨማሪ በተለያዩ መድረኮች፣ በሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም በትምህርት ቤቶች የትራፊክ ደንቦች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የትራፊክ ደንብ ጥሰቶችን መፈጸም ለተለያዩ አደጋዎች ምክንያት እየሆነ ነው ያሉት ምክትል ዳሬክተሩ፤ በከተማዋ ከፍጥነት በላይ የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች 52 በመቶ መሆናቸውን ገልጸዋል። ከሚደርሱ አደጋዎች 40 በመቶ የሚሆነው ደግሞ የአደጋው መንስኤ ከፍጥነት በላይ ማሽከርከር መሆኑን ተናግረዋል።

ባለሥልጣኑ ፍጥነትን ሊቆጣጠሩ የሚችሉ እንደ የፍጥነት መቆጣጠሪያ (ስፒድ ራበር) እና የፍጥነት መቀነሻ (ስፒድ ብሬከር) ላይ ማሻሻያ እየተሠራና ከማሻሻያ ያለፉት ላይ ደግሞ ቁጥጥር በማድረግ ርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ብለዋል።

በሁለተኝነት ለአደጋ መንስኤ ተብሎ የተመዘገበው ጠጥቶ ማሽከርከር መሆኑን ገልጸው፤ ይህንንም ለመከላከል ባለሥልጣኑ በቅርቡ 8 ሚሊዮን ብር በማውጣት የአልኮል መመርመሪያዎችን መግዛቱን ገልጸዋል።

ሌላኛው በከተማዋ ለአደጋ መንስኤ እየሆነ የሚገኘው የአሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪ ብቃት ማነስ መሆኑን የገለጹት አቶ አማረ፤ በከተማዋ ያሉ መኪናዎች ረጅም ዓመታት ያስቆጠሩ በመሆናቸው በተሽከርካሪ ብቃት ማነስ ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም ብለዋል።

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከአዲስ አበባ አሽከርካሪ ፍቃድ ቁጥጥር ባለሥልጣን ጋር ብቃት ያለው ተሽከርካሪና አሽከርካሪ እንዲኖሩ ለማስቻል ፍቃድ የሚሰጡ ተቋማት የተግባርና የንድፈ ሀሳብ ሥልጠናዎች በብቃት እንዲሰጡ በጋራ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

# በክልሉ በዘንድሮው የምርት ዘመን ከ82 ሺህ ቶን በላይ የቡና እሸት ተሰብስቧል

## -67 ሺህ ቶን የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል

**አመስወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡-በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በዘንድሮው የምርት ዘመን ከ82 ሺህ 400 ቶን በላይ የቡና እሸት መሰብሰቡን የክልሉ ቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ገለጸ። 67 ሺህ 348 ቶን የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ እቅድ መያዙም ተገልጿል።

በክልሉ የቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አሥራት መኩሪያ ለኢፕድ እንደገለጹት፣ በ2016 የምርት ዘመን ከ82 ሺህ 400 ቶን በላይ የቡና እሸት ተሰብስቦ ወደ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች ገብቷል።

በምርት ዘመኑ 106 ሺህ ቶን የቡና እሸት ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን እስካሁን ድረስ ባለው የመሰብሰብ ሂደት ከ82 ሺህ 400 ቶን በላይ የቡና እሸት ተሰብስቧል። የማሰባሰብ ሂደቱ ከአንዳንድ አካባቢዎች በስተቀር የተገባደደ ሲሆን ከጥር ወር ጀምሮ ደረቅ ቡና የማሰባሰብ ሂደት ይጀምራል ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት በዘንድሮ ዓመት 67 ሺህ 348 ቶን ለማዕከላዊ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል። ዘንድሮ የተሰበሰበውን ቡና የማጠብና የመቀሸር ሥራ ገና የሚከናወን ሲሆን እስካሁን ድረስ ለማዕከላዊ ገበያ 18 ሺህ 180 ቶን ቡና ቀርቧል።

በክልሉ ቡና የታጠበና ያልታጠበ ቡና እንደሚዘጋጅ በመጥቀስ፣ አጠቃላይ በክልሉ 249 የታጠበ ቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች እንዳሉ ተናግረዋል። 216ቱ ቅድመ ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ቡና ማጠብ ሥራ ገብተዋል። አብዛኞቹ የማጠብ ሥራቸውን እያጠናቀቁም ይገኛሉ ብለዋል።

በደረቅ መልኩ ለሚዘጋጅ የቡና ምርት 125 የቡና መቀሸሪያ ኢንዱስትሪዎች የሚገኙ ሲሆን፣ ቅድመ ዝግጅታቸውን በማጠናቀቅ በጥር ወር ወደ መቀሸር ሥራ ይገባሉ ሲሉ አስረድተዋል።

በክልሉ በአራት ዓይነት የቡና ማምረት ሂደት በጫካ፣ በከፊል ጫካ፣ በአልሚዎች እና በጓሮ ቡናን የማምረት ሂደት 560 ሺህ ሄክታር መሬት የቡና ማሳ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የቡና ማሳን የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ አሥራት፣ ችግኝ ከማዘጋጀት አንጻር በዘንድሮ ዓመት የተዘጋጀውን እና ከባለፈው ዓመት የተረፈውን ጨምሮ ከ75 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ተዘጋጅተዋል። ከሚያዝያ እስከ ሐምሌ ወር ባለው ለተከላ ይደርሳሉ ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት የቡና ዝርያ በማሻሻል በክልሉ እንዲተከል ከማድረግ በተጨማሪ የሲዳማ፣ የማዕከላዊ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ወስደው እየተከሉ ይገኛል።

በመጨረሻም ምርታማነትን ለማሳደግ ቡና የመጎንደል ኮምፖስት የማዘጋጀት ተግባር እየተሠራ ነው። በገበያ በኩል የሚያጋጥመውን ችግር ለመቅረፍ ከቡናና ሻይ ባለሥልጣን ጋር እየሠሩ እንደሆነ አስረድተዋል።

# በክልሉ በመጪው ክረምት 5 ነጥብ 5...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኤሊያስ ከድር ለኢፕድ እንደገለጹት፣ በዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር እንደክልል 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል የታቀደ ሲሆን አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

እስካሁንም 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኖችን ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን ችግኞቹ በአጠቃላይ 1 ነጥብ 15 ሚሊዮን ሄክታር ላይ ይተከላሉ። እነዚህ ለመትከል ከታቀዱት ችግኞች ውስጥ 11 በመቶ የሚሆነው ፍራፍሬና ቀርከሐ ችግኞች ናቸው ብለዋል።

እንዲሁም 12 ሺህ ኩንታል የተለያዩ የፍራፍሬ፣ የደንና ለከብቶች መኖ የሚያገለግሉ ዘሮችን ለማቅረብ ታቅዶ 11 ሺህ 800 ኩንታል ዘር ማቅረብ ተችሏል፤ 80 በመቶ የመትከያ ቦታ መለየትም መቻሉን አስታውቀዋል።

በመርሐግብሩ አምስት አይነት ችግኞች የሚተከሉ ሲሆን በአንድ ጀምበር አረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብርም 500 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል መታቀዱን አቶ ኤሊያስ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ችግኝ ጣቢያዎችን የማዘመን፣ የዘር እና ለችግኝ ጣቢያ ሊያገለግሉ የሚችሉ ግብዓቶችን የማማሏት ሥራ እየተሠራ መሆኑን አቶ ኤሊያስ ገልጸው፣ የዝግጅት ሥራው እስከ መጋቢት ወር ይጠናቀቃል ብለዋል።

አቶ ኤሊያስ እንደገለጹት በክልሉ ላለፉት 5 ዓመታት 18 ነጥብ 3 ቢሊዮን ችግኝ የተተከለ ሲሆን 88 ነጥብ 5 በመቶ ፅድቀት አለው። ይህም ከ17 በመቶ የነበረውን የደን ሽፋን ወደ 26ነጥብ6 በመቶ አሳድጓል። ምዕራብ ኦሮሚያና ማዕከላዊ ኦሮሚያ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን ስላላቸው ከፍተኛ የፅድቀት መጠን እንዳለባቸውም ገልጸዋል።

በጋ ላይ የሚሠራው የአፈር ልማትና ጥበቃ ሥራ የሚተከለው ችግኝ ወሳኝ ነው ያሉት አቶ ኤሊያስ፤ በዚህም ከአረንጓዴ ዐሻራ ጎን ለጎን አፈር እና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በትኩረት እንደሚተገበር አስታውቀዋል።

አቶ ኤሊያስ እንዳስታወቁት ‹አፈርንና ሀገርን ጠብቀን ተንከባክበን ለትውልድ እናሳልፍ ›በሚል መሪ ቃል የ60 ቀን አፈር እና ውሃ ጥበቃ ዘመቻ ሥራ እየተሠራ ነው።

በእነዚህ ተግባራት በአጠቃላይ 9 ነጥብ 8 ሚሊዮን የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚሳተፉ ሲሆን ይህም አገልግሎት በብር ሲተመን 9 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ይሆናል ብለዋል።

በዚህም የመሬት ምርታማነትን በማሳደግ የሚገኘው ሰብል በመጨመር ገበሬውን ተጠቃሚ የሚያደርግና የከርሰምድር ውሃ እና የተለያዩ ኩሬዎች በቅርበት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ነው።

በተጨማሪም ማኅበረሰቡ በተለያዩ ዘርፎች እንዲሠማሩ የሥራ እድል ለመፍጠርና ከገጠር ወደ ከተማ ያለውን ከፍተኛ ፍልሰት ለመቆጣጠር ያስችላል ብለዋል።

በመሆኑም ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል በአፈርና ውሃ ጥበቃ ብሎም በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር ላይ በመሳተፍ የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

# በኢትዮጵያ የመጀመሪያው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ ዋና አስተዳዳሪው ገለፃ፣ ፋብሪካው በተለይ ከውጭ የሚገቡ የታጠበ የድንጋይ ከሰል ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት ትልቅ ዕድል ይፈጥራል። የውጭ ምንዛሪ ዕጥረትን ለመቅረፍም የራሱ አስተዋፅዖ አለው።

የታጠበ የድንጋይ ከሰል ከውጪ በከፍተኛ ምንዛሪ እንደሚገባ ጠቅሰው፣ ፋብሪካው እስካሁን አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል ብለዋል።

የከሰል ማዕድን አምራቹ ኢቲ ማይኒንግ ፋብሪካ እንደሚሰኝ የተናገሩት ኃላፊው፣ ፋብሪካው ወደ ሙከራ ትግበራ እየገባ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል።

የኢቲ ማይኒንግ ድርጅት ተወካይ ወንድሙ ምትኩ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ ፋብሪካው የመጨረሻ አስፈላጊ የሚባሉት ነገሮች እየተገጠሙለት ይገኛል። በመገባደድ ላይም ነው።

እንደ አቶ ወንድሙ ገለፃ፣ ፋብሪካው ከሁለት ዓመት በፊት የተጀመረ ነው። በአሁኑ ጊዜ አጠቃላይ ሥራው እየተጠናቀቀ በመሆኑ በፋብሪካው የሚሠሩ ቋሚ ሠራተኞች ሥልጠና እየተሰጠ ነው። የሙከራ ሥራዎች ከተሠሩ በኋላ ከሁለት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ተመርቆ ሥራ ይጀምራል።

ኢትዮጵያ በቂ የከሰል ማዕድን እያላት ከደቡብ አፍሪካ በውጭ ምንዛሪ የታጠበ ከሰል ገዝታ እንደምታስገባ የገለፁት አቶ ወንድሙ፣ በተለይ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በዚህ ምክንያት ለከፍተኛ ወጪ ተዳርገዋል ብለዋል።

ይህ ፋብሪካ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን የታጠበ ከሰል ፍላጎትን 75 በመቶ የመሸፈን አቅም ያለው ነውም ብለዋል።

ፋብሪካው በሰዓት 150 ቶን የታጠበ ከሰል የማምረት አቅም እንዳለውም ነው የገለፁት።

የፋብሪካው ፕሮጀክት ማናጀር ኢንጅነር በላይ አሰፋ እንዳሉት፣ የኢትዮጵያ የታጠበ ከሰል ፍላጎት ሀገሪቱ በዓመት በአማካይ 400 ሚሊዮን ዶላር እያሳጣት ነው።

ኢቲ ማይንግ ፋብሪካ ሲጠናቀቅ ይህን ወጪ ማዳን ያስችላል ብለዋል።

ፋብሪካው 3 ሺህ 600 ቶን የታጠበ ከሰል በቀን የማምረት አቅም አለው ያሉት ኢንጅነር በላይ፣ በጥቂት የውጪ ሀገር እና በሀገር ውስጥ ሠራተኞች እየተገነባ መሆኑ ለሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ልምድ መካበት የበኩሉን አስተዋፅዖ ያበረክታል ብለዋል።

# “የጋራ ተጠቃሚነትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑን አመላክተዋል።

ስምምነቱ ጥቅማቸውን ሳይነካባቸውና ኢትዮጵያን እስከማውገዝ የደረሱ አንዳንድ ሀገራት ጉዳዩ ሳይመለከታቸው የሚሰጡት ነቀፋ ተቀባይነት አይኖረውም ሲሉ አምባሳደር ፍጹም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የምታደርጋቸው ማንኛውም ዓይነት ስምምነቶች የጋራ ተጠቃሚነትን መርሕ ያደረጉ መሆናቸውን በሁለትዮሽና በሌሎች የዲፕሎማሲ አማራጮች የማስረዳት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አንስተው፤ ይህም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል።

ለቀጣናው በማሰብ ሳይሆን ለራሳቸው ተጠቃሚነት ከመጨነቅ ስምምነቱን እያወገዙ የሚገኙ አካላትን ኢትዮጵያ በሰከነ ዲፕሎማሲያዊ መንገድ እያስረዳች መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በሰጥቶ መቀበል መርሕ የምታምን ሀገር ናት ያሉት አምባሳደር ፍጹም፤ ለቀጣናው ትስስር እያበረከተች ካለው አስተዋፅዖ በተጨማሪም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ትስስር መፍጠሯንም አስረድተዋል።

ከጎረቤቶቿ ጋር በንግድና መሠረተ ልማት የተሳሰረች እንዲሁም በጋራ ተጠቃሚነት የምታምን ሀገር መሆኗን ገልጸው፤ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ልትሰጥና ልትቀበል በምትችልባቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራት ስምምነት የማድረግ መብት እንዳላት አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የወደብ ስምምነት ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ ለማደግ፣ በመሠረተ ልማትና በንግድ የበለጠ ለመተሳሰር ለምታደርግው ጥረት አንዱ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የባሕር በር ተጠቃሚ መሆን መቻሏ የራሷን የገቢና ወጪ ምርት በመቆጣጠር የተሳለጠ የወደብ አገልግሎት ለማግኘት እንደሚያግዛት ገልጸው፤ በቀጣይም የገቢና ወጪ ምርቶችን በማሳደግ ተወዳዳሪ መሆን የሚቻልበትን የሎጂስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

እያደገ ለመጣው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የበርበራና የጂቡቲ ወደብ በቂ አለመሆናቸውን የተናገሩት አምባሳደር ፍጹም፤ ከሌሎች ሀገራት ጋር በጋራ ለመስራት የምትችልበትን አማራጭ መጠቀም ይገባል ሲሉ አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሽልማቱ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) ራዕይ ያከበረ፤ ትጋት ያገናዘበ ነው!

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሀገሪቱን በሁለንተናዊ መልኩ ወደ አዲስ ታሪካዊ ምዕራፍ ለማሻገር በመንግሥት በኩል ሰፊ ጥረት እየተደረገ ነው። በዚህም እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች ከሀገር አልፈው የዓለም አቀፍ እውቅና ምንጭ እየሆኑ ነው፤ በዓለም አቀፍ መድረኮች ሀገር ደምቃ እንድትታይ መልካም አጋጣሚዎችን እየፈጠሩ ነው።

አስቻጋሪ በሆኑ ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ውስጥ እየተተገበሩ ያሉ እነዚህ ስኬታማ የልማት ክንውኖች፤ መንግሥት ለልማት ያለውን ቁርጠኝነት ከማሳየት ባለፈ፤ በችግር ወቅት ሀገርን መታደግ የሚያስችል ስትራቴጂክ የአመራር አቅም/ብቃት ባለቤት እንደሆነ በተጨባጭ ማሰየት ያስቻሉ ተሞክሮዎች ናቸው ።

ከዛም በላይ ሕዝብና መንግሥት ተናብበው እና ተደማምጠው በሙሉ አቅማቸው መንቀሳቀስ ከቻሉ፤ እንደ ሀገር ያሉ ፀጋዎችን አውቆ በማልማት፤ የሀገርና የሕዝብን ነገዎች ብሩህ ማድረግ፤ የትናንት ስብራቶችን መጠገን እና መራመድ የሩቅ መንገድ ጉዞ እንዳልሆነ አመላካች ናቸው ።

በተለይም መንግሥት ከትናንት ጥቋቁር ታሪኮቻችን በመነሳት በምግብ እህል እራስን ለመቻል የጀመራቸው ስትራቴጂክ ጥረቶች፤ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆነው ስኬታማ የመሆናቸው እውነታ ለሕዝባችን አንድ የእፎይታ ምንጭ ከመሆን ባለፈ ፤ የዓለም አቀፍ እውቅና ምንጭ መሆን ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

በምግብ እህል በተለይም በበጋ የስንዴ እርሻ እየተመዘገበ ያለው ስኬት፤ አሁን ላይ እንደ ሀገር ያጋጠመንን የድርቅ አደጋ መቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር አስችሏል፤ እንደ ሀገር በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል የጀመርነው ጥረት አዲስ የታሪክ ትርክት ይዞ እየመጣ ስለመሆኑ አመላካች ሆኗል።

ሀገሪቱ ለስንዴ እርሻ ያላትን መሬት፣ የውሀ ሀብት፣ ቴክኖሎጂና የሰው ኃይል በማቀናጀት በጥቂት ዓመታት ውስጥ በመቶ ሚሊዮን ዶላር ከውጪ ይገባ የነበረውን የስንዴ ምርት በማስቀረት ብሎም እንደ ሀገር በዓለም አቀፍ የስንዴ ገበያ ውስጥ መግባት የሚያስችል ተስፋ ሰጭ ጅማሬ ላይ ትገኛለች ።

በገበታ ለሀገር እየተሠሩ ያሉ ሀገራዊ ሥራዎችም በጅምር ደረጃ የሚታዩ ቢሆኑም፤ በዚህ ደረጃ ያላቸው ውጤታማነት፤ እንደ ሀገር በምግብ እህል ራስን ከመቻል ባለፈ፤ ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ፤ በዚህም ጤናማ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ለሚደረገው ጥረት ተስፋ ሰጭ አቅም ናቸው ።

ይህ ሀገራዊ ፀጋዎችን ለይቶ፤ ወቅቱን በሚዋጅ ውጤታማ ስትራቴጂ እየታገዘ ተግባራዊ በመሆን ላይ ያለው በምግብ እህል ራስን የመቻል ሀገራዊ ንቅናቄ፤ ከዚህ ትውልድ ባለፈ የሚመጡ ትውልዶችን ከምግብ እህል ጠባቂነት የሚታደግ፤ በረሀብ የጎደፈውን የትናንት ታሪካችንንም የሚያድስ ነው።

በመንግሥትና በመላው ሕዝባችን ቅንጅት ውጤታማ እየሆኑ ያሉ ሥራዎች፤ ሰላማዊ በሆነ ሀገራዊ ዓውድ ውስጥ መተግበር የሚያስችል ዕድል ቢያጋጥማቸው የውጤታማነታቸው ደረጃ ከዚህም ሊበልጥ እንደሚችል፤ በዓለም አቀፍ መድረኮችም የበለጠ ደምቀን እንድንታይ አቅሞች ይሆኑን እንደነበር ለመገመት የሚከብድ አይደለም።

በምግብ እህል ከጠባቂነት ወጥተን እራሳችንን እንድንችል የጀመርነው ሀገራዊ ጥረቶቻችን፤ አሁን ከደረሱበት በላይ ብዙ እርምጃዎችን መራመድ የሚችሉበት፤ እኛም እንደሀገር የበለጠ ቀና ብለን የምንሄድባቸውን የተሻሉ ዕድሎች መፍጠር የሚያስችሉ እንደሆኑም ይታመናል ።

ይህንን ሀገራዊ ተጨባጭ እውነታ በአግባቡ በመረዳት፤ የስኬቱ ባለ ራዕይ ለሆኑት ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተባበሩት መንግሥታት የምግብ እና የእርሻ ድርጅት የከበረውን የፋኦ አግሪኮላ ሜዳሊያ መሸለሙ ተገቢ እና ተጠባቂ ጭምር ነው። ለጀመርነው በምግብ እህል ራስን የመቻል ሀገራዊ መነቃቃት ስኬት ትልቅ አቅም የሚሆን ነው።

ሽልማቱ በምግብ ዋስትና እና በተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ላሳዩት ራዕይ፣ አመራር እና ቁርጠኝነት፣ ብሎም ፈጣን፣ ተለዋዋጭ እና ፈታኝ በሆነው ከባቢያዊ ሁኔታ በስንዴ ምርት ራስን ለመቻል በተከተሉት ፈጠራዊ መፍትሔ ዕውቅና ለመስጠት የተበረከተ መሆኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ራዕይ ያከበረ ትጋት በአግባቡ ያገናዘበ ነው!።

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ተቀባይነትን በስፋት ለማሳደግ

**ምሕረት ሞገስ**

የጥሬ ገንዘብ ዝውውር እየወረደ የዲጂታል ባንክ አገልግሎት ማደጉ የተለያዩ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ እየተገለፀ ነው። የመጀመሪያው ጠቀሜታ በጥሬ ገንዘብ ለመላክ ሰፋ ያለ ጊዜ የሚጠይቅ ሲሆን፤ ገንዘብ አንቀሳቃሹ ባንክ ከመሔድ ጀምሮ የባንክ አገልግሎት ሰጪው ገንዘቡን ሲስተም ላይ እስከሚመዘግብ ድረስ የሚፈጀውን ጊዜ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት በእጅጉ አሳጥሮታል። በዲጂታል ባንኪንግ የባንክ ሠራተኛው ምንም ሳይሳተፍ ተገልጋዩ ባለበት ቦታ በላከበት ቅፅበት ተቀባዩ ጋር ይደርሳል።

የባንክ ተጠቃሚው በእጅ ስልኩ የወጣውን እና ያለውን የገንዘብ መጠን ማወቅ የሚችል በመሆኑም፤ የተለያዩ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ብዙ አይቸገርም። ይህ ሌላኛው ጠቀሜታው ነው ፤ የባንክ ደንበኛው በእጁ ጥሬ ገንዘብ ባይኖርም የፈለገውን አገልግሎትም ሆነ ቁስ በዲጂታል የባንክ አገልግሎት ተጠቅሞ መግዛት መቻሉም ቴክኖሎጂውን የበለጠ ተመራጭ አድርጎታል።

ከዚህም በላይ በፈለገው ፍጥነት ገንዘብ መላኩ፤ አገልግሎትም ሆነ ዕቃ መግዛቱ ሕይወቱን ቀላል እና ውጤታማ በማድረግ ነፃነቱን በማጎናፀፍ በኩል የሚኖረው አስተዋፅዖም የሚናቅ አይደለም።

የዲጂታል የባንክ አገልግሎት ከቀን ወደ ቀን ቴክኖሎጂውን ተከትሎ ተለዋዋጭነት እየታየበትም ነው። ቀደም ሲል በመልዕክት መረጃ በመላክ ይካሔድ የነበረው ልውውጥ አሁን በሶፍት ዌር በተሻለ ፍጥነት እና ቅልጥፍና እየተከናወነ ይገኛል። ግልጽነትን በመፍጠር በኩልም የዲጂታል የባንክ አገልግሎት እጅግ ተወዳጅነትን አትርፏል።

ገንዘብ ሲንቀሳቀስ ለምን ዓላማ ለማን ገንዘቡ እንደተላከ ቴክኖሎጂው መዝግቦ የሚይዝ በመሆኑ፤ በቀላሉ ያለምንም ክርክር ልውውጡን ማረጋገጥ ይቻላል። ከግለሰብ ባሻገር መንግሥት ለወረቀት ገንዘብ ማሳተሚያ የሚያወጣውን ወጪ ከመቀነስ በተጨማሪ ሌሎች ብዙ ጥቅሞች አሉት ።

ይህ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት የፋይናንስ አስተዳደርን ከሌሎች የንግድ ሥራዎች ጋር በማቀናጀት በዓለም ላይ ከፍተኛ ውጤት እያስገኘ ነው። በኢትዮ ጵያም በ2015 የበጀት ዓመት በዲጂታል የክፍያ አማራጮች የተንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን ከ4 ነጥብ 7 ትሪሊዮን ብር በላይ ደርሷል። ይህ የገንዘብ መጠን ከቀዳሚው ዓመት ከ2014 ዓመተ ምሕረት ጋር ሲነፃፀር በ3 ነጥብ 1 ትሪሊዮን ብር ብልጫ አለው ሲል ሪፖርተር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጠቅሶ አብራርቷል። ይህ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት እና የዲጂታል የግብይት ሥርዓት መጨመሩን የሚያሳይ ነው።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ለመቀነስ የተቀናጀ ሥራ እየተሠራ መሆኑም እየተነገረ ነው። ይህ በራሱ የዲጂታል የግብይት ሥርዓት እንዲስፋፋ የሚያስገድድ ሲሆን፤ ኅብረተሰቡ ለዲጂታል አገልግሎት ያለው የመቀበል ሁኔታም ጨምሯል። ነጋዴዎች በዲጂታል አማራጭ ገንዘብ ለመቀበል ፈቃደኛ እየሆኑ ይገኛሉ። የግለሰብ ተገልጋዮችም በዲጂታል ክፍያ ለመፈፀም ዝግጁ ሆነው ታይተዋል። በፊት አንድ አገልግሎትን ወይም ዕቃን ለመሸመት ኪሴን ልፈትሽ ይል የነበረ ዜጋ፤ አሁን በተንቀሳቃሽ ስልኬ ላይ ገንዘብ እንዳለኝ ላረጋግጥ እያለ ነው።

ሰዎች ለመጠባበቂያ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ላይ ገንዘብ ይዘው መንቀሳቀስ ከመጀመራቸው ባሻገር፤ የተሻሻሉ እና ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እየቀረቡ ናቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ የበለጠ ስኬታማ ለመሆን ባንኮች ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው የፋይናንስ ተቋማት ነጋዴዎችን መልምለው በቀለጠፈ መልኩ በዲጂታል ግብይት እንዲጠቀሙ የማሠልጠን ሥራ መከናወን እንዳለበት የዘርፉ ምሑራን በመናገር ላይ ናቸው ።

> **ችግሮቹን ለመከላከል የይለፍ መለያዎችን/ ኮዶችን መቀያየር እና የመግቢያ መረጃዎችን መጠበቅ እንደሚገባ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ**

የዲጂታል የባንክ አገልግሎት፣ የተንቀሳቃሽ ስልክ የገንዘብ ዝውውር ወይም የዲጂታል ግብይት ሥርዓት ዕድገት አስደሳች ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ በኔትወርክ መቆራረጥ ምክንያት እያጋጠመ ያለው ክፍተት መሻሻል እንዳለበት ። ከዚህም ባለፈ ዘርፉ ለተለያዩ ማጭበርበሮች ሊጋለጥ የሚችልበትም አጋጣሚ ብዙ ነው። ችግሮቹን ለመከላከል የይለፍ መለያዎችን/ኮዶችን መቀያየር እና የመግቢያ መረጃዎችን መጠበቅ እንደሚገባ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ።

በሌላ በኩል አገልግሎት ሰጪው አውቆም ሆነ ባለማወቅ ግብይቱን በዲጂታል መንገድ ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆነ፤ ጥሬ ገንዘብ ሳይዝ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት ተማምኖ የተንቀሳቀሰ ሰው የፈለገውን አገልግሎትም ሆነ ዕቃ ለመግዛት ይቸገራል። ከዚህም ባለፈ የተወሰነው የማኅበረሰብ ክፍል በተለያዩ ምክንያቶች በሞባይል ቴክኖሎጂ ገንዘባቸውን ሲያንቀሳቅስ ሌላው ደግሞ በተቃራኒው በቴክኖሎጂው ባለመተማመን ወይም በተለየ ወቅታዊ ችግር ወደ ኋላ ሊመለስ ይችላል፤ በዚህ ወቅት ባንኮች ሊፈጠር የሚችለውን ክፍተት ግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል ።

ይህንን እውነታ በአግባቡ ባለመረዳት ሰሞኑን በባንኮች በኩል የተፈጠረውን ችግር ማንሳት ይቻላል። በዓሉን አስመልክቶ በባንኮች አካባቢ የታየው ጥሬ ገንዘብ ላለመስጠት የነበረው ማንገራገር ደንበኞችን ቅር አሰኝቷል። አንዳንድ የግል ባንኮች «ለበዓል የዶሮ እና የበግ መግዣ የሚሆን ጥሬ ብር የለንም ግብይታችሁን በዲጂታል ፈፅሙ።» ብለው፤ ማስገደዳቸው ከፈረሱ ጋሪው ቀደመ ለማለት አስገድዷል።

ገበያው ላይ በበቂ መጠን ቴክኖሎጂው ተስፋፍቶ ከወረቀት የፀዳ ዝውውር ከመስፋፋቱ በፊት ደንበኛው ያስቀመጠውን ገንዘብ «በጥሬው አንሰጥም» ብሎ መከልከሉ፤ የገበያ ሥርዓቱን ችግር ውስጥ ከመክተት ባለፈ፤ ደንበኞች ገንዘባቸውን ባስቀመጡባቸው ባንኮች ላይ ያላቸውን አመኔታ ችግር ውስጥ የሚከተው ይሆናል፤ የባንክ ዘርፉንም ስጋት ውስጥ ሊጨምረው ይችላል ።

አንዳንድ ጊዜ በአጋጣሚ ከተፈጠሩ ችግሮች በመነሳት የባንክ ደንበኞች የዲጂታል የባንክ አገልግሎት ደህንነቱ ያልተጠበቀ ነው ብለው ሊወስዱ፤ በዚህም ስጋት ሊያድርባቸው ይቻላል። ከዚህ የተነሳም ግብይቱን በጥሬ ገንዘብ ማከናወን ምርጫቸው ሊሆን ይችላል ።

ባንኮች አጋጣሚዎች ሊፈጥሯቸው የሚችሏቸውን ችግሮች በአግባቡ በማጤን በአሠራራቸው ላይ ተገቢውንም ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። ከሁሉም በላይ ደንበኞቻቸው የዲጂታል የባንክ አገልግሎትን ተጠቃሚ እንዲሆን ማበረታታት ፤ በአገልግሎቱ መተማመን እንዲፈጥሩ ሰፊ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

## ነፃ ሃሳብ

# በብሄራዊ ምክክር - ከግጭት አዙሪት ለመውጣት

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገር ከምትጸናባቸው መንገዶች ውስጥ የተግባቦት ጽንሰ ሀሳብ ቀዳሚው ነው። ስልጣኔና የዘመናዊነት በትረ ጸዳሎች መነሻቸው ከሌላው ጋር እንዴት መኖር ይቻላል? የሚል ጽንሰ ሀሳብ ነው። በብዙ በርትተን ከሌሎች ጋር እንዴት መኖር እንዳለብን ካልገባን አላዋቂዎች ነን። በዓለም መንደር ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ እንዲሁም ከመሰል የፉክክር አውድ እኩል የልዩነትን ጎራ ይከፈለው ይሄ አስተሳሰብ ነው። በብዙ የሀሳብና የፍላጎት መናር ውስጥ እርቅና ምክክርን ያቀፈው ሁለንተናዊው ዓለም ‹ተግባቦትን› የዘመናዊነት ሚዛን ሲል ይጠራዋል። እርግጥ ነው ዘመናዊነት ከማሰብና ሀሳብን ለበጎ ነገር ከመጠቀም የሚጀምር ነው።

በሰው ልጅ የማሰብ አቅም ውስጥ ከተደረሱ ሊዕቀ እሳቤዎች ውስጥ ቀዳሚው በተግባቦት አብሮነትን ማስቀጠል የሚለው ነው። በምክክር አብረን መኖር ካልቻልን አብሮ ሊያኖረን የሚችል ሌላ ምድራዊ ኃይል የለም። አንዳንድ በባህልና በማህበረሰብ ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ አጥኚዎች ሀገርና ሕዝብን፣ ባሕልና ታሪክን የሚያቆራኙት በብዙሀነት ውስጥ በተውጣጣ የጋራ ሀሳብና ተግባቦት ነው። ይሄ ማለት የአንድ ሀገር ትላንትናዊ፣ አሁናዊና ነጋዊ ታሪክ የተወሰነውና የሚወሰነው ማሕበረሰብ ተነጋግሮ ለመግባባት ባለው ልምምድ ልክ ነው ማለት ነው።

ደግሞም እውነት ነው። ያለፉ ታሪኮቻችንን መለስ ብለን ብንቃኝ በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ልብ፣ በአንድ ግብር ጀምረን የጨረስናቸው ናቸው። አሁን ላይ እንደጥንቱ ጸንቶ መቆም አቅቶን የምንገዳገደው ደግሞ ድሮነትን ሽረን እኔነትን በማራመዳችን ነው። ይሄን እውነታ ለመረዳት ጠቢብ መሆን አይጠይቅም። ትላልቅ ድሎቻችን የትላልቅ ሀሳቦቻችን ውጤቶች እንደነበሩ መካድ አይቻልም። ፍሬ አፍርተው ዛሬም ድረስ ባለሞገስ ያደረጉን የታሪክ ገድሎቻችን በሰፊ ሸራ ላይ በአብሮነት የጻፍናቸው እንደሆኑ የሚታወቅ ነው።

ዛሬ የብቻ ታሪክ ለመጻፍ እሽቅድምድም ላይ ነን። ከመቶ ሚሊዮን ቅይጥ ሕዝብ ውስጥ፣ ከሰማኒያ በላይ ጉራማይሌ መልክ ውስጥ በብዙ ባህል፣ በብዙ ታሪክ በተሰናሰለ ማሕበረሰብ ውስጥ እንደምን እኔነት ይቻላል? ስለምን ብቻነት ታሰበ? ሊገባንና እንዲገባን የምፈልገው እውነት እዚህ ጋር ነው ያለው። ኢትዮጵያን የብሄረሰብ እናት፣ የባሕልና የታሪክ አምድ ካልን መነሻችን አንድነት ነበር ማለት ነው። መጀመሪያችን ፍቅርና ወንድማማችነት ነበር ማለት ነው። ታዲያ ይሄ አይነቱ የራስ ወዳድነት አባዜ በዚህ ሕዝብ መሀል ምን ይሰራል? በእኛነት በቅለን በእኔነት መራመድ እንደምን ይቻላል? ተደባልቆና ተቀይጦ ለመኖርና እየኖረ ላለ ማሕበረሰብ የታሪክ ሽርፈት ምን ይበጀዋል? ።

አለማወቅ የእውቀት ክፍተት ወይም ደግሞ ካለመረዳት የሚጀምር እንደሆነ ይታመናል። አለማወቅ ግን መነሻው አለመረዳት ወይም ደግሞ የእውቀት ክፍተት ሳይሆን ሆን ብሎ መሳት ከሆነ "አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም" እንደሚባለው ነው። ከዚህ የተነሳም አሁን ላይ ሁላችንም ወደራሳችን ልንመለከት ይገባል። ሀገርና ትውልድ፣ ሕዝብና ታሪክ ተሰናስለው በሚኖሩባት ኢትዮጵያ ላይ እየሄድንበት ያለነው መንገድ ምን ያህል እንደሀገር እንደሚጠቅመን ቆም ብለን እናስብ። ልዩነቶቻችንን አርቀን ወደተግባቦት የምናመራው በእውነትና ሁሉን ባማከለ አካሄድ ስንገኝ ነው።

እውነትን መሰረት አድርጎ መገናኘት ከፊታችን ላለው የተግባቦት መድረክ ጥሩ መነሻ የሚሆን ነው። ,ሀገራዊ ምክክር ሀገራዊ መፍትሄዎችን የምናመጣው ወደ ቀደመው የአብሮነት ከፍታ የምንሸጋገርበት የተሀድሶ ምዕራፍ ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ልዩነቶቻችንን አድርቀንና አጥበን በእርቅና በይሁንታ አዲሷን ኢትዮጵያ የምንፈጥርበት የድህነት መድረክ ነው። መድረኩ የምንፈልገውን እንዲሰጠን መድረኩ የሚፈልገውን ልንሰጠው ይገባል። መድረኩ የሚፈልገው የሀሳብ ልውውጥ ነው። ነጻና ገለልተኛ፣ የማንም ጣልቃ ገብነት የሌለው የምክክር ቦታ ነው። ልባችንን ለፍቅርና ለይቅርታ፣ ለእርቅና ለአብሮነት አስገዝተን ከሆነ ለእርቅ የተቀመጥነው መድረኩ የሚሰጠን ብዙ ነገር አለው።

ጥንተ አብሮነታችንን ያወየቡ የብሔርና የዘረኝነት ካባዎች መውለቅ አለባቸው፡ ወንድማማችነታችንን ያደበዘዙ የቡዳኔና የጎጠኝነት መንፈሶች መሚሸሽ አለባቸው። ብዙሀነታችንን ያሳነሱ የእኔነትና የብቻነት ደዌዎች መሻር አለባቸው። ሀገር በእኔነት ውስጥ የክብር አክሊል የላትም። ትውልድ በመለያየት ውስጥ የብኩርና በትር የለውም። ሕዝብ በመናቅ ውስጥ የፊተኝነት ዳና የለውም። መነሻዎቻችን የበጎነት መንፈሶች ከሆኑ የመድረሻ ምኩራቦቻችን የእኔነትን ነውር አይጸንሱም።

ላሉብንና ለሚኖሩብን ፖለቲካዊም ሆኑ ሌሎች የልዩነት ተግዳሮቶች ትልቅ መፍትሄ ሆኖ ከፊት የሚመጣው የምክክር ባሕል ነው። የእኛ ባሕል ጦርነት ነው። በጦርነት ማንም እንደማይችለን እየተነገርን ያደግንና ዛሬም ድረስ በዛ አስተሳሰብ ስር የወደቅን ነን። ይሄ ያለንበት ዘመን የኃይል ፖለቲካን፣ የኃይል ርምጃን ሽሮ ተግባቦት ላይ ደርሷል። አሮጌውን ሽረን በአዲሱ ማዕቀፍ ውስጥ እስካልገባን ድረስ ህልሞቻችን ለመኖር ጊዜ ይፈጅብናል።

በብዙ ጥያቄና ልዩነት ውስጥ በምትዳክር ሀገር ላይ የኃይል አስተሳሰብ የፍቅርን በር አይከፍትም። እንዳይከፈቱ ሆነው የተከረቸሙ የአብሮነት በሮቻችን በኃይል የዘጋናቸው እንደሆኑ ብናውቅ ምን ያክል ለተግባቦት ወደ ኋላ የቀረን እንደሆንን እንደርስበት ነበር። ሆደሰፊነትን ከትዕግስትና ከመቻል፣ ከምክክርና ከተግባቦት ጋር ያዋሃዱ ከፓርላማ ወደ ሕዝቡ፣ ከመንግስት ወደትውልድ የሚንጸባረቁ አንዳንድ ፖለቲካዊ ልምምዶች ያስፈልጉናል። ልምምዳችን የኃይል ሆነና የፍቅር በሮቻችንን ጠርቅሞብናል። እውቀታችን ራስ ተኮር ሆነና እኛነትን ሽሮብናል።

ንቅናቄአችን ለሁሉ የምትበቃ ሀገር መፍጠር ከሆነ ለሁሉ የሚበቃ አስተሳሰብና መረዳት ሊኖረን ይገባል። ከራስ ርቆ ሌሎችን መዋጀት በማይችል ስሜት ለበስ እውቀት ሀገር አትፈጠርም። በራስወዳድነት ያካበትናቸው ብዙ የጠበቡ ስርዐቶች አሉን። እነዚህ ስርዐቶች ሰፍተውና ገዝፈው ለሌላው እስኪበቁ ድረስ በሀሳብ፣ በልምድ፣ በእይታ፣ በምክክር፣ በእርቅ፣ በአቃፊነት፣ በአብሮነት መበርታት ለነገ የማንለው ጉዳይ ነው። ባንዳዎች እና ጽንፈኞች ያስተማሩን ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ ያረቡን ግን ደግሞ የሙጥኝ ብለናቸው የምንቆስልባቸውና የምንደማባቸው አንዳንድ ሽሾቶች አሉ።

እንደ አለመታደል ሆኖ ማሕበራዊ ልምምድ በፖለቲካዊ ልምምድ የሚፈጠር ነው። ልክ የሚሆነውና ሀገርን በስርዐት የሚያቆማት ፖለቲካ በማሕበራዊ ልምምድ ቢፈጠር የሚለው ነው። ፖለቲካ በማሕበራዊ ልምምድ ቢፈጠር መነሻ የሚያደርገው የሕዝቡን ባሕልና ወግ፣ ስርዐትና አስተሳሰብ ነው። ማሕበራዊ ልምምድ በፖለቲካዊ ልምምድ ሲፈጠር ግን መነሻው እኔነትና ራስወዳድነት፣ ውሸትና ማስመሰል ነው። ለዚህም ነው በተመቸ ሀገር ላይ ባልተመቸ ፖለቲካ የምንሰቃየው።

ከሀገር ፖለቲካ ከገዘፈ፣ ከሕዝብ ፖለቲከኛ ከበረታ ትልቁ አደጋ ያለው እዛ ጋር ነው። እንደ ሀገር ዋጋ እየከፈልንም ያለው ለዛ ነው። በብሄራዊ ምክክሩም ሆነ ቀጣይ በሚኖሩ የአብሮነት መድረኮች ላይ የጋራ ስምምነቶች እንዲኖሩ በሕዝብ አስተሳሰብ የታነጸ ፖለቲካ ያስፈልገናል። በሕዝብ አስተሳሰብ የተቃኘ የፖለቲካ ምህዳር ሁሉን አቃፊ፣ ለማሕበረሰቡ ባሕልና እሴት የሚገዛ ነው። ዝም ብሎ ማሰብ ሳይሆን ሀሳባችን የቆመበትን፣ እግሮቻችን የረገጡበትን አውድ መቃኘት ያስፈልጋል። ምክንያታዊ ሳይሆኑ እና የእይታ አድማስን

> **በሰው ልጅ የማሰብ አቅም ውስጥ ከተደረሱ ሊዕቀ እሳቤዎች ውስጥ ቀዳሚው በተግባቦት አብሮነትን ማስቀጠል የሚለው ነው። በምክክር አብረን መኖር ካልቻልን አብሮ ሊያኖረን የሚችል ሌላ ምድራዊ ኃይል የለም**

ሳያሰፉ ማሰብ ራስን ለተመሳሳይ ጥፋት ከመዳረግ ውጪ ወደፊት አያራምድም።

የተስፋዎቻችን ምስራቅ ብርሀን ሊረጩ እኛን እየጠበቁ ነው። ጥላቻ ያጨለማቸው የአብሮነት ቀንዲሎቻችን ንጋትን ሊያበስሩ የእኛን አብሮ መቆም የተጠባበቁ ነው። የመሸብን ስላልተያያዝን ነው። የረፈደብን ስለተራራቅን ነው። አንድ መሆን እስካልቻልን ድረስ ብዙ ማጥና ድጦች ይጠብቁናል። ብዙ ኖሮን ምንም እንደሌለው የሆነው የፍቅር ኩራዛችንን ስላጠፋን ነው። ዳግም እንድናብብ በኢትዮጵያዊነት ማዕድ ፊት ዳግም መፈጠር ይኖርብናል።

ነቅተንና በቅተን፣ አውቀንና ገብቶን ሀገር ለማቆም ካልተነሳን የሚያንገዳግደን ብዙ ነው። ስለሆነም ስለሰላምና ፍቅር እያሰማናቸው ያሉ የእርቅ ድምጾች ጎልተው መሰማታቸው አለባቸው። አንድነትን ለመውለድ እያደረግን ያለነው ትግል ያለዝለት ከፍጻሜ መድረስም አለበት።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሀሳብ ልውውጥ በኩል የዳመነ ማንነታችንን ለማጥራት ብዙ ተጉዞ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱ ይታወቃል። የምክክር መድረኮችን ከማዘጋጀት ጀምሮ የልየታ ስራዎችን በማጠናቀቅ ለተግባቦት በሩን ከፍቶ እየጠበቀን ነው። ኮሚሽኑ ስራ ሲጀምር አብረውት ሊሰሩ ፍቃደኝነታቸውን ያሳዩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር አነስተኛ እንደነበር የሚታወስ ነው። አሁን ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ የሁሉም ይሁንታን አግኝቷል።

በዚህ መልክ በጋራ ምክር የጋራ መፍትሄ ሊያመጣ ዝግጅቱን ጨርሷል። ይሄ የሚያሳየው እንደኮሚሽን የሄደበትን ረጅም ርቀት ነው። እኛም የራሳችንን ግዴታ በመወጣት ለሰላም በተከፈተው በር ውስጥ አልፈን አሻራችንን ማሳረፍ ይጠበቅብናል። ብርቱዎች ሁልጊዜም በፍቅርና በምክክር የልቦናቸውን በር የሚከፍቱ ናቸው። በይቅርታና በአብሮነት ለዘወትር ተኝተው የሚነቁ ናቸው።

እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን የሚል አንድ ወገን የረገጠ ጽንፈኝነት በታሪካቸው ውስጥ የለም። ስለሆነም ከሌሎች ጋር አብሮ ለመኖር አይቸገሩም። በተቃራኒው ብርታታቸውን በእልህና በቁጣ የተቀዳጁ እነሱ ከሌላው ጋር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያልተረዱ፣ ከሌላው ጋር ሳይዛመዱ የራሳቸውን ሀሳብ ብቻ የሚያራምዱ እኔዎች ናቸው። ስለሆነም በታሪካቸው ውስጥ ፍቅርና አብሮነት፣ አንድነትና ሕብረት የለም። ስለዚህም ራሳቸውን ከሌላው ጋር አስማምተው ለመኳዝ ይቸግራቸዋል።

ይሄን ግለሰባዊ እውነታ ወደሀገር ስናመጣው አሁን ላሉብን ብሄራዊ ውጥንቅጦች እንደመስተዋት መሆን የሚችል ነው። በእኛም ሀገር መሰል ነገር መስተዋል ከጀመረ ሰነባብቷል። በጋራ ቤት ውስጥ የብቻ ታሪክና መሰል ሀሳብ የለም። እንዳመጣጣችን አካሄዳችንም ተያይዘንና ተደጋግፈን መሆኑ ለሰላማችን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ጸንተንና በርትተን እልፍ ሽምድምድ ሀገራትን ያበረታነው ሀገርን አስቀድሞ ሰውነትን ባስከተለ የአብሮነት መንፈስ ነው። እንደሰንደቅ ከፍ ብለን በሌላው ልብ ውስጥ በነጻነት ፋናወጊነት ስንውለበለብ ዓለም ያውቀናል። እንደዋርካ ገዝፈን ለሌሎች ጥላ መሆን የጋራ ታሪካችን ነው።

ስልጣኔውን ሰላም ተኮር ያላደረገ የፖለቲካ ስርዐት እንዴትም ቢበረታ መዛሉ አይቀርም። የሰላም እጦት ባለመግባባት የሚመጣ እንደሆነ ሁሉ አብሮነትም በመግባባት የሚመጣ ነው። በመነጋገርና በመመካከር ልዩነቶችን መፍታት ያልተለማመደ ሀገርና ሕዝብ በልዩነቱ ከመጠቃት ባለፈ እርባና አይኖረውም። እንደ ቱባ ክር የመከራዎቻችንን ጫፍ ይዘን የተለተልናቸው የታሪክና የልዩነት ጽንፎች ብዙ ናቸው። እንዲነጋልን ለአንድነት በተከፈቱ የእርቅ በሮች ስር እንለፍ። ከሁሉ በላይ ከግጭት አዙሪት ለዘለቄታው ልንወጣ የምንችለው ቁጭ ብለን ስንመካከር ብቻ መሆኑን ልንረዳው ይገባል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## “ስማርት ኮርት ሲስተም” - የፍትሕ ሥርዓቱን ለማዘመን

ዲጂታል ኢትዮጵያ እውን የማድረጉ ጉዞ ከተጀመረ ቅርብ ጊዜ ቢሆንም፣ ጉዞውን የሚያፋጥኑ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፤ ይህን ተከትሎም ለውጦች እየታዩ ናቸው። በተለይ ተቋማትን በማዘመን የአሰራር ሥርዓቶችን ወደ ዲጅታል የመቀየር ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመላክተው፤ የመንግሥት ተቋማት አገልግሎቶችን ዲጅታላይዝድ ከማድረግ አኳያ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። በዚህም እንደ ሀገር 528 የሚሆኑ የለሙ የዲጅታል አገልግሎት መስጫዎች ተግባራዊ ተደርገዋል።

ዜጎችን ላልተገባ ወጪና እንግልት ሲዳርጉ የቆዩ አብዛኞቹን አሰራሮች የመቀየር ተግባር እየተከናወነ ሲሆን፤ በዚህ ዲጅታል አሰራር በኩል እየተከናወነ ባለው ተግባር የተቀላጠፈና የተሳለጠ አገልግሎት መስጠት እየተቻለም ይገኛል። በተለይ ብዙ ተገልጋዮች የሚስተናገዱባቸው ዜጎችን ለምሬትና ለቅሬታ የሚዳርጉ አገልግሎቶች ዲጅታል ከተደረጉ በኋላ ችግሮች በብዙ መልኩ ተፈትተው ዜጎች በቀላሉ በዲጅታል አገልግሎት ተጠቀመው ቀልጣፋ አገልግሎት እያገኙ ነው።

አሁንም ዲጅታላይዜሽን በመስፋፋት ሁሉንም ተቋማት ተደራሽ ለማድረግ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ተገልጋዩ አገልግሎቶችን በቀላሉ እያገኘ ካለበት ሁኔታ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው። ወደዚህ አሠራር ሳይገቡ የቆዩ ተቋማት አሁን ወደ አገልግሎቱ እየገቡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል በተለይ ዜጎች ለአላስፈላጊ ውጭ ሲዳረጉባቸው ከቆዩባቸው ምሬትና እንግልት እንዲሁም ተደጋጋሚ ቅሬታ ያቀርብባቸው ከነበሩትና የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያዘምኑ ሲፈለጉ ከነበሩት ተቋማት መካከል የፍትሕ ተቋማት ይገኙበታል።

በተለይ ፍርድ ቤቶች ከአገልግሎት አሰጣጣቸው ጋር ተያይዞ የአገልግሎት ጥራት ጉድለት ሲስተዋልባቸው መቆየታቸው ይታወቃል። አሰራራቸውን በማዘመን ዜጎች የሚፈልጉትን አገልግሎት በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያደርግ ስርዓት መከተል ዘመኑ የሚጠይቀው ተግባር ሆኗል። የዚህ አሰራር እውን መሆን ዜጎችን ከእንግልትና ከአላስፈላጊ ውጪ በመታደግ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል።

በቅርቡም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት በጋራ የፍትሕ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚያስችል “ስማርት ኮርት” የተሰኘ የቴክኖሎጂ ውጤት መተግበሪያ ይፋ አድርገዋል። ኢንስቲትዩቱ በሁሉም ዘርፎች ላይ ችግር ፈቺ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ምርቶች ተደራሽ በማድረግ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል። በዚህም ባለፉት ሦስት ዓመታት የጤና፣ የትራንስፖርት፣ የፋይናንስና ሌሎች የአገልግሎት ዘርፎችን ለማዘመን የሚረዱ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አበልፅጓል።

ይህንን ሥራ በማስቀጠል የፍትሕ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማበልፀግ ችሏል። ተቋሙ ለሀገር እድገት እንቅፋት የሆነውን የፍትሕ መጎደል ለማስቀረት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ውጤቶት ሰርቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስረክቧል።

ኢንስቲትዩት ያበለጸገው “ስማርት ኮርት”የተሰኘው መተግበሪያ የፍርድ ሂደቱን ሊያዘገዩ የሚችሉ ሁኔታዎችን በማስቀረትና ጊዜን በመቆጠብ በችሎት ወቅት አሁናዊና ታአማኒነት ያላቸው መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለመያዝ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን መረጃን ማቅረብ የሚችል የሰው ሰራሽ አስተውሎት ውጤት ነው።

ይህ ቴክኖሎጂ ‹‹በቨርችዋል ኮርት›› በመጠቀም ዳኞችና ጠበቆች በአካል መገኘት የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በያሉበት ሆነው በቪዲዮ ኮንፍረንስ አማካኝነት በርቀት እንዲገናኙ ማድረግ የሚያስችል ነው። ከዚህ በተጨማሪ የርቀት ምስክርነት መቀበል ወይም ምስክሮች ቨርችዋል በሆነ መልኩ ቃላቸውን የሚሰጡበት ሥርዓት፣ ዲጅታል የሰነድ ማስተዳደሪያ ሥርዓት፣ በችሎት ወቅት ደረጃቸውን የጠበቁ ምስሎችና ድምጽ መያዝ የሚያስችሉ፣ በችሎት ክርክር ወቅት የተቀረጹ ድምጾችን ወደ ጽሁፍ መቀየርና ሰነዶችን ማዘጋጀት የሚያስችሉ መተግበሪያዎችንም የያዘ ነው።

**ይህ ቴክኖሎጂ ‹‹በቨርችዋል ኮርት›› በመጠቀም ዳኞችና ጠበቆች በአካል መገኘት የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በያሉበት ሆነው በቪዲዮ ኮንፍረንስ አማካኝነት በርቀት እንዲገናኙ ማድረግ የሚያስችል ነው**

በዚህ መተግበሪያም ስድስት ሺ 44 ሰዓት የሚፈጅ የድምጽ ቅጂ፣ ሶስት ሺ 590ሰዓት የሚፈጅ የድምጽና የጹሑፍ ቅጂ፣ እንዲሁም ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዓረፍተ ነገሮችን ለግብዓትነት አገልግሎት ማዋል ያስችላል።

“ስማርት ኮርት” በፍርድ አሰጣጥ ሂደት ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን በጊዜና በሁኔታ ያልተገደበ ዘመናዊ የፍርድ ሥርዓትን ለዜጎች ለመስጠት ይጠቅማል። ዘመናዊ የችሎት ክፍል/ስማርት ኮርት ሩም/ ያለው ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በወረቀት ይቀርቡ የነበሩትን ፋይሎች ዲጅታይዝድ በማድረግ የፍርድ ሂደቱ ዘመኑ በደረሰበት የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ እንዲመራ ማድረግ የሚያስችል ነው።

ዘመናዊ የችሎት ክፍል ያለው ቴክኖሎጂ፣ የተለያዩ የዲጅታል መተግበሪያ ቁሶችም ተካተውበታል። በእነዚህ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የክስ ፋይሎችን መሰነድ የሚያስችል አገልግሎት ይሰጣል። ይህ የዲጅታል መረጃ አያያዝ በፍርድ ቤቶች በተለምዶ የሚያዝ (በማንዋል በሚጠቀሙበት ወቅት) የሚከሰተውን የፋይል መጥፋትና የመረጃ መዛባት ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረትም ይጠቅማል።

እነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የፍትሕ አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽና ዘመኑን የዋጀ ይሆን ዘንድ በኢትዮጵያ አርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች በጥንቃቄ የተሰሩ ናቸው። የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ካሜራዎች፣ ትላልቅ ስክሪኖች እና የድምጽ ቅጂን ማስቀረት የሚችሉ ኦዲዮ ሪከርደሮች ታዳሚዎችን የሚያሳትፍ ግልጽ ችሎት ለማድረግ ፋይል መያዝ የሚችልም ነው። በችሎት ወቅት የፍርድ ውሳኔንና የተከራካሪን ድምጽ ቀድቶ ወደ ጽሑፍ መቀየር የሚያስችል መተግበሪያ ያለው መሆኑን የኢንስቲትዩት መረጃ ያመላክታል።

ቴክኖሎጂው ይፋ መደረጉን አስመልክቶ በተዘጋጀው መድረክ ላይ ንግግር ያደረጉት የአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎት የቴክኖሎጂ አብዮት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ቁልፍ ምዕራፍ የሚፈጸምበት በዓለማችን ታሪክ አዲስ ገጽታ ጭምር መሆኑን አስታውቀዋል፡

ለፍትሕ ሥርዓቱም ተደራሽ መሆን ካለባቸው ታላላቅ ዘርፎች ይህ የሰው ሰራሽ አስተውሎት አንዱ መሆኑን ገልጸው፤ አሁን ያበለጸገው “ስማርት ኮርት ሲስተም” የፍትሐ ሥርዓቱን ወደ ሽግግራዊ ለውጥ እንደሚመራም ያመለክታሉ። ‹‹ቴክኖሎጂዎች የዳኝነት ሥርዓቱን ወደ ሽግግራዊ ለውጥ የሚመሩና በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የታገዘ ቀልጣፋ የዳኝነት ሂደትን ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው›› ሲሉ ይገልፃሉ።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ ወደ ሥራ ከገቡት መተግበሪያዎች በተለይ ንግግር ወደ ጽሁፍ የሚቀየር መሳሪያ የዳኝነት ሥርዓቱን ቀልጣፋ በማድረግና ሥራን በማቃለል ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። ይህ ሥርዓት በችሎት ሂደት የሚቀርቡ የቃል ክርክሮች ምስክሮችን ጨምሮ አጠቃላይ የችሎት ሂደቱን ወዲያውኑ ወደ ጽሁፍ በመቀየር ግልባጭ ለዳኞች ማቅረብ የሚያስችል ነው።

ሌላኛው ዘመናዊ መልዕክት መለዋወጫ (ስማርት ቻትፖት) ለተገልጋዮች በቀላሉ በዘመናዊ ስልካቸው ወይም በኮምፒዩተር አማካኝነት ያለ ገደብ መረጃ የሚያቀርብ ከሰዎች ንክኪ ነጻ የሆነ ቴክኖሎጂ ነው። ይህም ተገልጋዮች መደበኛ የቢሮ ሰዓት ሳይገድባቸው የትኛውም የሕግ ትርጉምን የተመለከቱ መረጃዎችን ጨምሮ ሌሎች ጉዳዮች ለመያዝ የሚያስችል አማራጭ እንደሚፈጥር የሚገልጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የመልዕክት መለዋወጫ አገልግሎቱ መረጃን ከማድረስ ባሻገር የተገልጋዮችን ቅሬታ የሚያስተናግድበት ሥርዓት የተበጀለት መሆኑንም ነው ያመላከቱት።

የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት በበኩላቸው፤ ዘመኑን የዋጀውን ይህንን ‹‹የስማርት ኮርት›› ቴክኖሎጂ ተግባራዊ በማድረግ ከፍትህ እጦት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት እንደሚቻልም ይገልጻሉ።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ሲስተሙ የፍትህ ሥርዓቱን እጅግ ዘመናዊ፣ የዳኝነት ሥርዓቱን ቀልጣፋና ተደራሽ ማድረግ ያስችላል። ለተቋሙ የለሙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ ንግግር ወደ ጽሁፍ የሚቀይር ሥርዓት (እስፒች ትራንስክራይብ ሲስተም)፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ችሎት/ስማርት ኮርት ትሩ/እና ዘመናዊ የውይይት መለዋወጫ ሮቦትና ኢንፎርሜሽን ዲስክ መረጃ መስጫ/ ስማርት ቻት ፖት/ ናቸው። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ወደ ሥራ ሲገቡ በዳኝነት ሥርዓቱ ላይ ጥራት ያለውና የተቀላጠፈ የፍትሕ ሥርዓት ካለማግኘት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችን በእጅጉ ይቀንሳል።

መተግበሪያው ዘመናዊ ዳኝነት ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችል ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ አቶ ቴዎድሮስ፤ የለማው ሥርዓት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሽግግራዊ ለውጦችን ለማምጣት እንደሚያግዝ ያመላክታሉ።

ይህ “ስማርት ኮርት” መተግበሪያ የመንግሥትና የተገልጋዩ ሀብትና ጊዜ ሳይባክን ተገልጋዩ ለአላስፈላጊ እንግልትና ወጪ ሳይዳረግ ጥራት ባለው መልኩ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ በሁሉም ፍርድ ቤቶች አገልግሎት ላይ እንዲውል እንደሚደረግ አመላክተዋል። መተግበሪያው አገልግሎት ላይ እንዲውል ሲደረግ የዳኞችን ሸክም እንዲያቀል ያደርጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

የዳኝነት አገልግሎቱን ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ተደራሽ የሚያደርገው ከመሆኑም በላይ አስተዳደራዊ ችግር መፍቻዎች በመረጃ ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ያስችላል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዘመኑ የደረሰባቸው ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ ማዋላቸው ፍትሕ የሰፈነባት፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚደረገውን ጉዞ ያግዛል ሲሉ ይናገራሉ።

በሥራ ላይ መዋል የጀመሩት ቴክኖሎጂዎች ዳኞችንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የስራ ጫናና የፍርድ ቤቱን ወጪ በመቀነስ ሥራን የማቀላጠፍ ሚናቸው ከፍተኛ መሆኑንም ገልጸው፤ ቀሪዎቹን ቴክኖሎጂዎች የማልማትና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ስራዎችን በማጠናቀቅ ፍርድ ቤቶችን ወረቀት አልባ ለማድረግና አገልግሎቶችን ለባለጉዳዮች ምቹት እንዲሰጡ የሚደረጉ ጥረቶች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ያስረዳሉ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ በመድረኩ ላይ እንደተናገሩት፤ መንግሥት የአገልግሎት አሰጣጡን ጨምሮ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ በቴክኖሎጂ የታገዙ ቀልጣፋ አሰራሮች እየተዘረጉ ናቸው። በ“ስማትር ኮርት” የተደገፈ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት መጀመሩ እንደ ሀገር ተስፋ ሰጪ ምእራፍ ላይ መሆናችንን ያመለክታል ሲሉም ጠቅሰው፣ በተለይ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ሙሉ በሙሉ ስኬታማ እንደሚሆን እርግጠኛ የሚያደርግ ነው ይላሉ።

የዳኝነት አገልግሎት አንድ ሀገር ውስጥ የሕግ የበላይነት እንዲከበር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ሥር እንዲሰድና የአገር ልማትና ብልጽግና እንዲሳካ ወሳኝ ስለመሆኑ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም ያሉት አቶ ታገሰ፤ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ለዜጎች ዋስትና መሆናቸውንና ጥንቃቄ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታሉ። ይህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው የዳኞች አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ፣ ግልጽ፣ ጥራት ያለው፣ ተገማችና ተዓማኒነት ያለው ሲሆን ብቻ መሆኑንም ያስገነዝባሉ።

የዳኝነት አገልግሎትን ለማሳለጥ የለሙት ሥርዓቶች በራስ በጀትና የባለሙያዎች አቅም የለሙ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይህም ሀገራችን ብዙ ተስፋ ሰጪ እምቅ አቅም እንዳላት እንደሚያመለክት ነው አቶ ታገሰ የገለፁት።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# አርብቶ አደሩ በእንስሳት ሀብቱ እንዴት ተጠቃሚ ይሁን ?

**ስምስም መንግሥቱ**

ውሃ እና ግጦሽ ፍለጋ ከብቶቹን ይዞ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሰው አርብቶ አደር ዛሬም በአየር መዛባት ምክንያት ከሚያጋጥመው ድርቅ እንስሳቱን ለመታደግ ቀዬውን ለቆ ይሄዳል። በአካባቢ ላይ የሚከሰቱ ግጭቶችም የአርብቶ አደሩ ሌላው ፈተና ነው። እንስሳቱን ወደ ኢኮኖሚ ጥቅም በማዋል በኩልም ክፍተቶች ይስተዋላሉ። እንዲህ ያለው ችግር ሶማሊያ፣ ኬኒያ በመሳሰሉ ጎረቤት ሀገሮች ውስጥም ተመሳሳይ ችግሮች ያጋጥማሉ።

በተፈጥሮ መዛባት እያጋጠመ ያለው የዝናብ እጥረት፣ የድርቅ መደጋገም በተለይ ለአርብቶ አደሩ ማሕበረሰብ የእለት ተእለት ኑሮ የከፋ እያደረገው በመምጣቱ ቀጠናውን ያስተሳሰረ መፍትሄ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህም በባሕል፣ በታሪካና በሕዝብ ለሕዝብ ትስስር የማይነጣጠለውን በጋራ መድረክ በማገናኘት የመፍትሄ ጥረቱ ተጀምሯል።

ለዚህም አንዱ ማሳያ በየዓመቱ የሚካሄደው አርብቶ አደሮችን መሠረት ያደረገ ሲፖዚየም ነው። ሰሞኑንም 19ኛው የአርብቶ አደሮች ቀን «አርብቶ አደርነት የምሥራቅ አፍሪካ ሕብረ ቀለም» በሚል መሪ ቃል በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ ተከፍቷል። ጥረቱ ግን ከዚህም በላይ መሆን እንዳለበት ይጠበቃል።

የአፋር ክልል ፕሬዚደንት ጽህፈት ቤት ውስጥ በአማካሪነት እየሰሩ የሚገኙት አቶ አህመድ ያሲን ዊሊሳ፤ እንደሚያስረዱት አርብቶ አደሩ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ በሚያጋጥሙት ችግሮች በአንድ ቦታ ተረጋግቶ እንዳይኖር አድርጎታል። በተለይ ደግሞ ከራሱ በላይ ለእንስሳቱ ቅድሚያ ስለሚሰጥ ለእንስሳቱ መኖ እና ውሃ ፍለጋ ቀዬውን ለቆ ይሄዳል። በዚህ የተነሳም የልማት ተጠቃሚ ሳይሆን ኑሮውም ሳይቀየር ዘመናት ተቆጥረዋል። ትኩረት የሰጠው ባለመኖሩ ኑሮው በየዘመናቱ ተመሳሳይ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በአርብቶ አደሩ መንደሮች ለውጦች እየታዩ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ አህመድ፤ የከብት ጭራ ተከትሎ የሚሄድ አርብቶ አደር መባል እየቀረ መሆኑንም የአፋር ክልልን ተሞክሮን ለአብነት ጠቅሰዋል። ዳመናን ተከትሎ መሄድ ሳይሆን፤ በአንድ ቦታ ተረጋግቶ ዘመናዊ የእንስሳት አረባብ ዘዴን እየተለማመደ መሆኑንና በአካባቢው ላይ የከብት መኖ እያዘጋጀ እንስሳቱን መመገብ መጀመሩን አስረድተዋል።


አርብቶ አደር የሚባለው ማሕበረሰብ አሁን ከፊል አርሶ አደር እየሆነ መሆኑንም ገልጸዋል። «በፀይ መውጫ ምሥራቅ አፍሪካ ደረጃ ሲፖዚየም መዘጋጀቱ ለአርብቶ አደሩ የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል። የአንዱ ችግር የሌላውም ጭምር ነው። መተባበር አለብን» በማለት ይገልጻሉ።

እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፤ በአፋር ክልል ከዚህ ቀደም ያልተለመደ የልማት ሥራ እየታየ ነው። አፋር በእርሻው በቆሎ፣ ሰሊጥ ካልሆነ በእንስሳቱ ነው በስፋት የሚታወቀው፣ አሁን ላይ በአፋር ክልል የግብርና ሥራ የለም የሚለው ብሂል ታሪክ ሊሆን እየተቃረበ ነው።

ስምጥ ሸለቆን ተከትሎ እንደ ሀገር እየተከናወነ ባለው የበጋ መስኖ ልማት አፋር ክልል ውስጥ የስንዴ ልማት በስፋት እየተከናወነ ይገኛል። ጤፍን ጨምሮ የተለያዩ የሰብል ልማቶች መልማት ጀምረዋል። በዚህ መልኩ እየተከናወነ ያለው የልማት ሥራ ለክልሉም ለሌላው ተአምር እየሆነ መምጣቱን ይናገራሉ።

አቶ አህመድ እንዳብራሩት፤ ክልሉ ቅድሚያ እየሰጠ ያለው ከእርዳታ እራስን ለማውጣት በምግብ እህል እራስን መቻል ላይ ነው። በዚህም ለውጦች እየተመዘገቡ ነው። በኢትዮጵያ የሰሜኑ ክፍል ተካሂዶ በነበረው ጦርነት አለመረጋጋት ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም፣ የአካባቢውን ሰላምና ፀጥታ በማስጠበቅ ልማቱን ተጠናክሮ መቀጠሉንም አስረድተዋል።

በምሥራቅ አፍሪካ በይነመንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) አርብቶ አደሮችና የእንስሳት የቆላማ አካቢዎች ልማት ማዕከል ዳይሬክተር ዶክተር ደረጀ ዋቅጅራ በበኩላቸው፤ የኢጋድ ሀገራት 70 በመቶ የሚሆነው፤ ቆላማና በዝናብ ለሚከናወን እርሻ ምቹ ያልሆነ ነው። ከዚህ ይልቅ አካባቢው ለእንስሳት እርባታ በጣም ምቹ ነው። በዚህ የተነሳም በቀጠናው ክልል ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ይገኛል።



አቶ አህመድ ያሲን ዊሊሳ



ዶክተር ደረጀ ዋቅጅራ

ይህን ከፍተኛ ሀብት ይዘው የሚገኙት የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ደግሞ በስፋት የሚገኙት በድንበር አካባቢ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ በምሥራቅ አፍሪካ በሚገኙ ሀገሮች መካከል ላይ የምትገኝ በመሆኗ ብዙ ሀገሮችን ታዋስናለች። በሚያዋስኗት ሀገሮች አብዛኛው በሚባል ደረጃ ተመሳሳይ የሆነ ቋንቋ፣ ባሕል፣ የኑሮ ዘይቤ ያላቸው ናቸው። ይህ አይነቱ ተመሳሳይነት ደግሞ የቀረበ ዝምድናን ፈጥሯል።

እንዲህ ያለው ነገር ደግሞ ለልማት፣ የአካባቢ ሰላምን ለማስፈን፣ በአጠቃላይ በማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች አንድነትን ለመፍጠር ምቹ ሆኖ ይገኛል። እንዲህ ያለው ምቹ ሁኔታ ያለው በአርብቶ አደሩ ማሕበረሰብ ውስጥ ነው።

አርብቶ አደሩ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ የሚገደደው ለእንስሳቱ መኖና የመጠጥ ውሃ ፍለጋ ነው። አርብቶ አደሩ የሚኖርባቸው አካባቢዎች ባለው የተፈጥሮ ሁኔታ ታስቦበት ከብት መኖ ስለማይመረት ብዙ አርብቶ አደሮች አቋርጠው ለመሄድ ይገደዳሉ። ድንበር አቋርጠው ሲሄዱ ትብብርና ድጋፍ የሚያገኙትን ያህል ግጭትም ይገጥማቸዋል። እንስሳቶቻቸውም ለተላላፊ በሽታ ይጋለጣሉ። ስለዚህም አርብቶ አደሩ ተረጋግቶ ሕይወቱን እዲመራ ለእንስሳት መኖ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

ሌላው የአርብቶ አደሩ ችግር በእንስሳቶታቸው የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ተግዳሮት ከሆነባቸው አንዱ የመሠረተ ልማት አለመሟላት ነው። ወደ ማዕከል ገበያ ለማምጣት የመንገድ ችግር ያጋጥማቸዋል። በዚህ የተነሳ ከፍተኛ የሆነ የገበያ ትስስር ችግር አለባቸው።

ገበያ ተኮር የሆነ የአመለካከት ክፍተትም ሌላው ተግዳሮት ነው። ሸጦ ለውጦ ሕይወትን ለመለወጥ የሚደረገው አናሳ ነው። አብዛኞቹ የእንስሳት ሀብት ባለቤት መሆናቸውን ብቻ ነው የሚያስደስታቸው። ስለዚህም አርብቶ አደሩ በዘመናዊ ግብይት ላይ በቂ ስልጠና እና ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ነው።

የአየር መዛባትና ከዚህ ጋር ተያይዞ ድርቅ በተደጋጋሚ መከሰቱ አርብቶ አደሩን ለኢኮኖሚ ችግር እየዳረገው ነው። ለተከታታይ ዓመታት በሚከሰት ድርቅ አንድ ቤተሰብ እስከ ሶስት መቶ እንስሳቱን ያጣበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።

አንድ ቤተሰብ እስከ ሶስት መቶ ድረስ እንስሳት ካለው፤ አጠቃላይ የሀብት መጠኑ ከፍተኛ መሆኑን ያመላክታል። ይህን ሁሉ የእንስሳት ሀብት ይዞ መቀመጥ ለሁሉም አደጋ አለው፤ የአርብቶ አደሩንም ሆነ፣ የሀገር ተጠቃሚነትን በማሳጣት፣መሬትን በማራቆት ነው ጉዳቱ የሚገለፀው። እንስሳቱ ወደ ገበያ ሲወጡ ግን ቀሪ እንስሳት መኖ ሣር ለማግኘት ነፃ መሬት እንዲኖር ያስችላል። ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትም ከፍ ይላል።

የአርብቶ አደሩን የእንስሳት ሀብት ወደ ኢኮኖሚ በመለወጥ እነርሱም ሀገርም ተጠቃሚ እንዲሆን ሥራዎች መሰራት አለባቸው። ኢጋድም አርብቶ አደሩ በእንስሳቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆን ነው ግፊት እያደረገ የሚገኘው

እንዲህ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት፣ የአርብቶ አደሩን የእንስሳት ሀብት ወደ ኢኮኖሚ በመለወጥ እነርሱም ሀገርም ተጠቃሚ እንዲሆን ሥራዎች መሰራት አለባቸው። ኢጋድም አርብቶ አደሩ በእንስሳቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆን ነው ግፊት እያደረገ የሚገኘው። ለዚህም እየተከናወኑ ካሉት ሥራዎች ለፖሊሲ አቅጣጫና ድጋፍ የሚሆኑ ተግባራት ይጠቀሳሉ።

ለአብነትም አርሶ አደሩ ለእንስሳቱ የሚሆን መኖ ከገበያ ላይ መግዛት ቢፈልግ አቅርቦቱ የለም። በዚህ በኩል ያለውን ክፍተት ለመቅረፍ ስትራቴጂክ የሆነ የመኖ ክምችት ያስፈልጋል። በአርብቶ አደሩ አካባቢ ከእንስሳት ሀብት በተጨማሪ ወደ ሀብትነት ሊቀየሩ የሚችሉ ሌሎች የሀብት ክምችቶች ይገኛሉ። ማር፣ ለሳሙና እና ለተለያዩ ግብአቶች የሚውሉ እጽዋትን እንዲሁም እጣን አምርቶ ለገበያ ማቅረብ ይቻላል።

እነዚህ ሀብቶችን በአግባቡ በመምራት ተጨማሪ ጥቅም እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል። አሁን ባለው ሁኔታ በአካባቢው ግንዛቤ ባለመፈጠሩ ያለውን ዛፍ ቆርጦ ለከሰል በማዋል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ ጉዳት የማድረስ ችግር ነው የሚስተዋለው። ለችግሮች መፍትሄ ሰጥቶ ውጤታማ ለመሆን ክልሎችን ማስተሳሰር ያስፈልጋል።

በአርብቶ አደሮች ቀን፣ ቢያንስ ስድስት ሀገራት ተሳትፈዋል። በሚካሄደው ሲምፖዚየምም ለአርብቶ አደሩ ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ ምክክሮች ይካሄዳሉ። ውይይቱ ጥልቅ እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር የሚካሄድ በመሆኑ፣ አርብቶ አደሩን ወደፊት ሊያራምዱ የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮችና ምክረሀሳቦች ይነሳሉ።

እንዲህ ባለው መንገድ የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለመቀየር የመንግሥታት ቁርጠኝነትና በፖሊሲ ዙሪያም ያለውን ሁኔታ በተመለከተም ዶክተር ደረጀ እንዳብራሩት፤ ሂደቱ ረጅም ቢሆንም ጅማሮዎች አሉ።

በቆላማ አካባቢ የሚኖሩ የአርብቶ አደር ማሕበረሰቦች ለምን በድርቅ ይጎዳሉ?፣ ከእርዳታም እንዲወጡ ሥራዎች ለምንስ አይሰሩም ? በሚል ቁጭት እኤአ 2011 ትልቅ የውይይት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ነበር።

በዚህ ፕሮግራም መነሻ በኢጋድ በኩል ብዙ ሥራ ተሰርቷል። የገበያ ዕድልም ተፈጥሯል። የእንስሳት ሕክምና ተቋማትም ተከፍተዋል። በዚህ ወቅት የተፈጠሩ መነሳሳቶች ናቸው ከኬኒያ ተነስቶ ሞያሌ ለመግባት ሰሶት ቀናትን ይወስድ የነበረውን ጊዜ በአንድ ቀን ማሳጠር የተቻለው።

ኢትዮጵያም እስከ ሞያሌ ድረስ አስፓልት ለማድረግ የተነሳሳችው የጋራ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ነው። የዛሬ አስር ዓመት አካባቢ ከዩጋንዳ ወደ ከረሞጃ የሚባል አካባቢ ለመሄድ ሁለት ቀናት ጊዜ ይወስድ ነበር። በዚያ ላይ እስከ ሕይወት ማጣት የሚያደርስ ስጋትም ነበር። በመንግሥት በተደረገ ርብርብ መሠረተልማት በመዘርጋቱ ስጋቶች ተቀርፈዋል። ይህን ተከትሎም ለእንስሳት ንግድ ምቹ ሆኗል።

«እኔ እኤአ በ2015 ደቡብ ኦሞ አካባቢ እንስሳትን በበቆሎ ነበር አርብቶ አደሩ ቀይሮ የሚጠቀመው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓለም ባንክ ጋር ባደረገው ትብብር በተለያዩ ቦታዎች ገበያዎችን በማቋቋም ለችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ጥረት አድርጓል» ሲሉም ዶክተር ደረጀ የመንግስትን ጥረት አድንቀዋል።

አርብቶ አደሩ የሚኖርባቸው አካባቢዎች ካላቸው የመሬት ስፋት አንጻር በልማት ለማዳረስ ጊዜ የሚወስድ እንደሆነ የጠቆሙት ዶክተር ደረጀ፤ በመንግሥት በኩል ፍላጎቱ መኖሩን ግን አረጋግጠዋል። ወደፊት፣ ወደኋላ የሚሉ ነገሮች እንዳይኖሩ፤ የምሥራቅ አፍሪካ የእንስሳት ሀብት ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረጉን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ይላሉ።

የተጀመረውን ሥራ ወደፊት ለማራመድና በፖሊሲም እንዲደገፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አመልክተዋል።

ኢጋድ ክፍተት በሚስተዋልባቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ለፖሊሲ ግብአት የሚሆን የጥናት ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ደረጀ፤ «ለአብነትም እንስሳት ከምግብነት ባለፈ ለማዳበሪያ፣ የእርሻ መሳሪያም ሆኖ በማገልገል ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳለውም ከፍ ያለ ግንዛቤ ባለመያዙ በሁሉም ሀገራት ዘንድ ለእንስሳት ዘርፍ የሚደረገው ኢንቨስትመንት አነስተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአርብቶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻል የተሰጠው ትኩረት መልካም በሚባል ሁኔታ ላይ እንዳለና ተጠናክሮ ከቀጠለም ስኬቶችን ማስመዝገብ እንደሚቻል ነው ከአስተያየት ሰጪዎቹ መረዳት የሚቻለው። በተለይም ቀጠናውን ያስተሳሰረ እንቅስቃሴ ለውጤት እንደሚያበቃም ነው የገለጹት።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## የማሕበራዊ ሚዲያ ጥቃት ሰለባዎች

አስመረት ብስራት





የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው። እድሜያቸው ከአስራ አምስት እስከ አስራ ሰባት የሚገመት አፍላ ወጣቶች ናቸው። በሚማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ከአንደኛ ደረጃ ጀምረው አብረው ስለተማሩ መለያየት ይከብዳቸው ነበር። ከሰፈር ሲወጡ አንስተው ትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ እስኪደርሱ ድረስ አይለያዩም ነበር። ከልጅነታቸው ጀምሮ ተመሳሳይ ትምህርት ቤት በመማራቸው እንደ ወንድምና እህት ነበር የሚተያዩት። በልጆቹ ፍቅር የተነሳ ቤተሰቦቻቸው ተግባብተው ወዳጅ ሆነዋል።

ማጥናቱንም መማሩንም አብረው ሲያደርጉት የቆዩ ልጆች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሲሆኑ ሌሎች ጓደኞች ወደ ቡድኑ ቀላቀሉ። መጀመሪያ አካባቢ ጥሩ ቢሆንም ቀን ቀንን እየወለደ ሲሄድ ልጆቹ ከክፍል መቅረት ብሎም አጓጉል ባህሪዎችን ማሳየት ጀመሩ።

ወንዶቹና ሴቶቹ ልጆች አብረው በማደጋቸው መለያየት ባይፈልጉም በአዋዋላቸው መለያየት ምክንያት የጓደኝነት ቡድኑ ለሁለት ተከፈለ። ቀን ቀንን እየወለደ ለወራት የተለያዩት ጓደኛሞችን ይበልጥ የሚከፋፍል ነገር ተፈጠረ። እቤት ሆነው የሚሰሩትን አሳይመንት መምህር ካዘዛቸው በኋላ አንድ ለጥናት የሚመች ቦታ እንዳለ እና እዛ ሄደው የቤት ስራቸውን መስራት እንደሚችሉ አዲስ ወደ ቡድኑ ከተቀላቀሉት ልጆች ሀሳብ ይመጣል።

ሀሳቡ አሳማኝ ስለነበረ በእረፍት ቀናቸው ለየቤት ስራው የሚሆኑ መፅሀፍቶችና ደብተራቸውን ሸክፈው፤ በተቀጣጥሩበት ሰዓት ተገናኝው ወደ ቦታው ይሄዳሉ። ሴቶቹ ልጆች አብሮ አደግ ወንድ ጓደኞቻቸው ስላሉ ምንም ሳይሳቀቁ ነበር ወደ ቦታው ያቀኑት። በቦታው እንደደረሱ የአካባቢው ጭር ማለት ሴቶቹን ቢያሰጋቸውም ከወንድሞቻቸው እኩል የሚመለከቷቸው ወንድ ጓደኞቻቸው በመኖራቸው ቀለል ብሏቸዋል። እንደሄዱ ኮካ መሰል መጠጥ አይምሯችንን ነፃ እንዲያደረግን በማለት ጠጡ። ከዛም ወንዶቹ በወረቀት የተጠቀለለ ነገር ማጨስ ጀመሩ። ያን ጊዜ ሴቶቹ ራሳቸውን መቆጣጠርም መከላከለም በማይችሉበት ደረጃ ተዳከሙ። መዳከማቸውን የተመለከቱት ወንዶች ማድረግ የሚፈልጉትን ነገር ለማድረግ ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ ተጠቃቅሰው ተነሱ።

ከዛ በኋላ አብሮ አደግ ጓደኞቻቸውና አዲስ አብረዋቸው የተቀላቀሉት ጓደኞቻቸው ተራ በተራ ወሲባዊ ግንኙነት ፈፀሙባቸው። ከሀገራችን ባሕል የወጡ፤ የማሕበረሰቡን እሴት ያልተከተሉ ከተለመደው ውጪ የሆኑ ነገሮችን ሲያደርጉ በቪዲዮ እየቀረፁ ነበር። ከዛ በኋላ ያንን ቪዲዮ እያሳዩ ደግመን ካላደረግን ገመናችሁን ፌስ ቡክ ላይ እንለቀዋለን በማለት በማስፈራራት ልጆቹን የማይገባ ሕይወት ውስጥ ከተቷቸው። ደጋግመው ግንኙነት እንዲያደርጉ ከማስገደድም አልፈው ለተለያዩ ሱሶቻቸው ማስፈፀሚያ እንዲሆን ገንዘብ ከየትም አንዲያመጡ ያስገድዷቸው ጀመር።

የቤት ስራ ለመስራት በሚል ሰበብ ከቤታቸው የወጡት ገና በአስራዎቹ እድሜ አጋማሽ ላይ የሚገኙት ሴት ልጆች በየዕለቱ ከማይፈልጉት ሰው ጋር ግንኙነት ከማድረግም አልፎ የአደንዛዥ ሱስ ተጠቂ ሆኑ። በትምህርት ሰዓት ከቤታቸው ቢወጡም ያገኙትን ገንዘብ ይዘው በሱስና በወንዶቹ ልጆች አስገዳጅነት ያልሆነ ቦታ መዋል ጀመሩ።

አሁን ላይ ልጆቹ በተፈጠረባቸው ሁኔታ የተነሳ ትምህርታቸውን መማር ያቃታቸውና በስነ ልቦና የተጎዱ መሆናቸውን የሰማነው ታህሳስ 4 ቀን 2016 ዓ/ም አዲስ አበባ የዘንድሮውን የ16ቱ ቀናት የጸረ ጾታ ጥቃት ንቅናቄ ማጠቃለያ አስመልክቶ በተካሄደ ውይይት ወቅት ነበር።

በመድረኩ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ጽንሰ ሀሳብ፣ የጥቃት አይነቶችና መንስኤዎች፣ ታዳጊና ወጣት ሴቶች የሚገጥሟቸው ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና የሚያደርሱት ስነ ልቦናዊ እና አእምሯዊ ተጽዕኖ፣ ጥቃቶችን ማስቆም በሚቻልባቸው መንገዶች፣ በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ ገለጻ ከተደረገ በኋላ የተለያዩ ሀሳቦች ከተሳታፊዎች ተንጸባርቀው ውይይት ተደርጓል። ተሳታፊዎችም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው የሚገጥሟቸውን ልምዶች አካፍለዋል።

በውይይት መድረኩ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ ታዳጊና ወጣት ሴቶች፣ ወጣት ወንዶች እንዲሁም የሚዲያ ባለሙያዎችና ተወካዮች የተሳተፉ ሲሆን ከላይ ያነሳነውና ሌሎች ተመሳሳይ ታሪኮች ሲነሱ ውለዋል።

ከተነገሩት ታሪኮች መካከል በወንድና ሴት ጓደኝነት መካከል በሚደረግ የፍቅር ግንኙነት ወንዱ ልጅ ከጓደኛው ጋር መኝታ ክፍል ውስጥ በመምጣት ሴቷ ለፍቅር ብላ በነፃነት የሆነችውን በሙሉ ቀርፆ በዩትዩብ በመልቀቅ የልጅቷን ሕይወት ወዳልተፈለገ ሁኔታ ያስገባበትም አጋጣሚ መኖሩን የሕግ ባለሙያ የሆኑት የመድረኩ ተሳታፊ ተናግረዋል።

ዩትዩብ ላይ ለሚገኝ ክፍያ ሲባል ሴቶቹ በላወቁበት ሁኔታ የተቀረፁ ቪዲዮዎችን መልቀቅ፤ በተለያዩ ምስሎችን ከማሕበራዊ ሚዲያ ላይ በመውሰድ እነሱ በላደረጉት ሁኔታ የተቀነባበሩ ቪዲዮችን በማሰራጨት የበርካታ ሴት እህቶችን ሕይወት የሚረብሹ ተግባሮች እየተከናወኑ መሆኑን ሰዎቹም በሕግ አግባብ ሊጠየቁ የሚችሉበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑን የሕግ ባለሞያዋ አብራርተዋል።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከሌሎች ወጣት ማሕበራት የተውጣጡት ወጣቶች እንደተናገሩት በወጣትነት ጊዜ ላይ መልካቸውን እየቀያየሩ የመጡትን ጥቃቶች ለመከላል ሁሉም ሰው በጋራ መስራት ይገባዋል። ይህም ማለት ወጣቶችን የሚያነቃቁ መድረኮችን ማዘጋጀትና ራሳቸውን ከጥቃት እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ማስተማር የግለሰቦችም በዘርፉ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎቸም ኃላፊነት መሆኑን በውይይቱ ላይ አንስተዋል።

በብዛት ጥቃት አድራሾችም በተለያዩ የስነ ልቦና ችግሮች የተጠቁ የሚሆኑበት ጊዜ ከፍተኛ መሆኑን የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች አንስተው ጥቃት አድራሹም የደረሰበት የስነ ልቦና ጉዳት ታክሞ ጠቃሚ ዜጋ ይሆን ዘንድ የመንግስት የስነ ልቦና ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ኃላፊነት ይኖርበታል።

ለሁሉም ወጣት በቀላሉ በጓደኝነትና በስርአት ሊያደርገው የሚችለውን ነገር በኃይልና በፀያፍ ሁኔታ ለማድረግ መሞከሩ የስነ ልቦና ችግር መሆኑን ተወያዮቹ አስረድተዋል። ይህ ዘመን አመጣሽ ማሕበራዊ ሚዲያ ተፅእኖም ከወጣቶች መካከል እንዲወጣ አስተሳሰብ ላይ በተገቢው መልኩ መሰራት እንደሚገባው በመድረኩ ላይ ተነስቷል።

የስርአት ፆታ ባለሙያ የሆኑት ወይዘሮ መስከረም ተካ በበኩላቸው ፆታዊ ጥቃት የምንላቸው በርካታ ናቸው። ጥቃቶቾ ፆታዊ፤ ስነ ልቦናዊ፤ አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ጥቃቶች በተለያየ ሁኔታና በተለያዩ አይነት ሰዎች ሊደርሱ ይችላሉ። ይህም ማለት ባልታወቁ ሰዎች ወይም በቅርብ ሰዎች፤ በስራ ቦታ ወይም በትምህርት ቤት፤ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ጥቃት አድራሾቹ ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም ጥቃት ይፈፅማሉ።

" በአብዛኛው ጥቃቶች ቤት ውስጥ ሊፈጠር ይችላል። ይህ አይነት ጥቃት ደግሞ ከሚደርሰው ማሕበራዊ ጫና አንፃር እየታየ ኀብረተሰቡ ይታገሰዋል። በሃገራችን የሴቶች ጥቃት በየጊዜዉ ብናወራበትም፤ ቀላል ቢመስለንም፤ ሁሉ ሰው ኃላፊነቱን ቢወጣ ሊቀረፍ የሚችል ይመስላል እንጂ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እየሆነ ያለዉ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ አይነቱ እየጨመረ ነዉ የመጣዉ" ይላሉ ባለሞያዋ።

ጾታዊ ጥቃት እየጨመረ የመጣዉ ማኅበረሰቡ ወንድን የሚያስቀድም በመሆኑ፤ ከባሕል አስታኮ የመጣ መሆኑ፤ በኢትዮጵያ የሚታየውን ብሎም ተባብሷል የተባለውን የፆታዊ ጥቃትን ለማስቀረት ግን በርካታ የሚመለከታቸው አካላት የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ መሆኑን ነው የሚናገሩት።

«አሁን አሁን በሃገሪቱ ውስጥ በሴቶች ላይ የሚደርሰዉን ጥቃት አይቶ፤ ሕግ ይከበርላቸዉ፤ መንግሥት ተገቢውን ትኩረት ይስጣቸዉ፤ ፍትሃዊነት ይኑር ብዬ አንድ ሺ ጊዜ ስናገረዉ የነበሩትን ነገሮች መድገም አልፈልግም፤ አልችልምም። የሚያዋጣዉ ራስዋን ያበቃች ሴት የሚፈጥሩ፤ በሴቶች ጉዳይ ላይ አለን የሚሉ በሴቶች ጉዳይ ላይ እንሰራለን የሚሉ፤ ተምረናል የሚሉ፤ ሰብዓዊነት ግድ ይለናል የሚሉ፤ ፖለቲከኛ ነን የሚሉ በጋራ ሲንቀሳቀሱ ነው፡» ሲሉ አስረድተዋል።

እንዳጠቃላይ ይህንን ብናነሳም በጣም እየተባበሰና ባልተለመደ ሁኔታ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ የመጣው የማሕበራዊ ሚዲያ ጥቃት የሚመለከተው አካል ቁጥጥር ካላደረገበት የሚያስከትለው ማሕበራዊ ጫና ቀላል አንደማይሆን የስርአተ ፆታ ባለሞያዋ ይናገራሉ።

**በተቀነባበሩ ቪድዮችና ምስሎች የተነሳ የፈረሱ ትዳሮች፤ በፍቅር ጓደኞቻቸው ከህደት ተፈፅሞባቸው በተለቀቁ ቪዲዮች የተነሳ ራሳቸውን ያጠፉ ወጣት ሴቶች፤ ከመዋረድ መሰደድ ይሻላል ብለው ብን ብለው የጠፉ ወጣት ሴቶች መኖራቸውን የስርአተ ፆታ ባለሙያዋ ይናገራሉ**

በተቀነባበሩ ቪድዮችና ምስሎች የተነሳ የፈረሱ ትዳሮች፤ በፍቅር ጓደኞቻቸው ከህደት ተፈፅሞባቸው በተለቀቁ ቪዲዮች የተነሳ ራሳቸወን ያጠፉ ወጣት ሴቶች፤ ከመዋረድ መሰደድ ይሻላል ብለው ብን ብለው የጠፉ ወጣት ሴቶች መኖራቸውን የስርአተ ፆታ ባለሙያዋ ይናገራሉ።

ለሁሉም ጥቃቶች መነሻ ከማሕበረሰበ ስለሚቀዳ ማሕበረሰቡ ቀድሞ የነበረውን ባሕልን አክብሮ የመኖር፤ ግብረ ገብን ለልጆቹ የማስተማር ነገርን ቅድሚያ ቢሰጥ መልካም ይሆናል። የወንዶች የበላይነት የሚታይበት ሁኔታንም ማስተካከል፤ ቤት ውስጥ የሚደርሱ ጥቃቶችንም ለመከላከል የጋራ ጥረት ማድረግ ተገቢ እንደሆነ የስርአተ ፆታ ባለሙያዋ ይናገራሉ።

ከዓለም ጤና ድርጅት በተገኘ መረጃ መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሦስት ሴቶች መካከል አንዷ በሕይወቷ ውስጥ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ይደርስባታል ይላል። በዚህ የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ መሰረት እድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ የሆነ 736 ሚሊዮን ያህል ሴቶች ጥቃት ደርሶባቸዋል ማለት ነው።

ሪፖርቱ እንደሚያመለክተው በጎርጎሮሳውያኑ 2020 የዓለም የጤና ድርጅት ከሠራው ጥናት ወዲህ የተጎዱ ሴቶች ቁጥር በአብዛኛው ባይለወጥም ይሄኛው ግን ጥቃት የሚጀምረው ገና በልጅነት መሆኑን አመልክቷል። እድሜያቸው ከ 15 እስከ 24 ዓመት ከሆኑት አራት ሴቶች መካከል አንዷ ዕድሜዋ እስከ ሃያዎቹ አጋማሽ እስኪደርስ በቅርብ አጋሯ ጥቃት ይደርስባታል።

ሰው ከእንስሳ የሚለይበት ሰብአዊ ክቡሩን ጠብቆ ሊያደርግ የሚገባው የፍቅር ግንኙነት በኃይል ማድረግ ከአንድ ሰው ነኝ ከሚል ግለሰብ የማይጠበቅ መሆኑን የሚያስረዱት የመድረኩ ተሳታፊዎች እነዚህን ጉዳዮች ቸል ማለት የማይገባ መሆኑን አስረድተዋል።

መልኩን እየቀያየረ የሚደረገው የሴት ልጅ ጥቃት ሀይ ባይ ያስፈልገዋል። ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸው የሕግ አከላት ፤ ሁሉም የማሕበረስብ አባላት፤ የሀይማኖት አባቶችም ሆኑ ሌሎች ይሄንን ችግር ለመቅረፍ በጋራ ርብርብ መስራት ይገባዋል በማለት የዛሬውን አበቃን። ከጥቃት የፀዳች ሀገር ትኖረን ዘንድ ምኞታችን ነው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**በድሮው አዲስ ዘመን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ አንባቢያኑ አንባቢ ብቻም ሳይሆኑ ተሳታፊም ነበሩ፡፡ ዛሬ ላይ ይህን ናፍቀን "ለምን?" ብንል፣ ምናልባትም የቴክኖሎጂና የሚዲያውን መብዛት ሰበብ እናደርግ ይሆናል፣ ምክንያት ግን አይደለም፡፡ አውቶብሱን በእንቅልፍ ሰመመን፣ የመነጥሩ ጣጣ፣ ይድረስ ለ"ኮንዶም" ተጠቃሚዎች፣ ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ፣ ስሜን ሰረቀና ለፈገግታ ... ልዩና የማይዘነጋ የአንባቢያን የሀሳብ ባሕር አለ፡፡ የዛሬው ዓምዳችንም ከእነዚሁ የአዲስ ዘመን ተሳታፊና አንባቢያን ደብዳቤዎች ላይ ያርፋል፡፡**

### አውቶብሱን በእንቅልፍ ሰመመን ሲነዳ

"ከጠጡ አይንዱ" የሚለው የማስጠንቀቂያ አባባል የቆየና በየአጋጣሚው የሚሰማ ጠቃሚ ማሳሰቢያ ነው፡፡

...

ሐምሌ 14 ቀን 1979 ዓ.ም ከጅማ ወደ አዲስ አበባ የተጓዘውን የጎን ቁጥር 768 የሆነውንና በልማድ "አይናፋር" በመባል የሚታወቀውን የአንበሳ አውቶብስ ያሽከረክሩ የነበሩት ሾፌር ይታይባቸው የነበረው አስጊ ሁኔታ ነው፡፡ ሾፌሩ ከሚዛን ጅማ ገብተው አዳር ሲሆን ማምሻውን ጠጥተው እንደነበርና በቂ እንቅልፍ አለማግኘታቸውን፤ ከብዙ ፈተና በኋላ በዕለቱ ወሊሶ ደርሰን ለዕረፍት በቆየንበት ቦታ ራሳቸው ሲናዘዙ ሰምቻለሁ፡፡ በጉዞ ላይ የእንቅልፍ ፍላጎት እያናወዛቸው በተደጋጋሚ ከአደጋ አፋፍ ላይ ሲያደርሱን ነገሩ ያሰጋቸው ረዳትና ተቆጣጣሪ ቀዝቃዛ ውሃ፣ ዙርባ ጫትና ሲጃራ ቢያቀርቡላቸውም ብዙ ሳይረዳቸው በመቅረቱ ተሳፋሪው በጭንቀት እንደተዋጠ ወሊሶ ሊደርስ ችሏል፡፡

ከሁሉም ይበልጥ የሚያሳዝነው ከተሳፋሪዎች መካከል በሹፌሩ ላይ ይታይ ስለነበረው ድካምና የእንቅልፍ ስሜት አንስተው ሲያሳስቡ እንዴት ተነካሁ በሚል እልህ መሪውን ከወዲያ ወዲህ እያሉት በበቀል ስሜት ተሳፋሪውን ማስጨነቃቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ መታየት ያለበት በዕለቱ ደህና መግባታችን ሳይሆን ሾፌሮች ከዚህ ተግባር እንዲቆጠቡ ምክር ሊሰጣቸው ይገባል ነው፡፡

(አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 19 ቀን 1979 ዓ.ም)

### የመነጥሩ ጣጣ

በኒውዮርክ ክፍለ ግዛት የሮቸስተር ከተማ ነዋሪ የሆኑት ፔርሲ እርር ድብን ያደረገቻቸውን ባለቤታቸውን ጥላቸው ስትሔድ አሳደው ከመንገድ ላይ በጥይት ይገድሏታል፡፡ ከዚያም ወደ ዘመዶቻቸው ቤት ሔደው ፖሊስ ጠርተው እጃቸውን ለመስጠት ይወስናሉ፡፡ ፖሊሶቹ ሲደርሱ ባለቤታቸውን የገደሉ መሆኑን ቢያስታውቁም የገደሏት ሴት ግን ባለቤታቸው ሳትሆን ሌላ ሴት መሆኗ ታውቋል፡፡ ድርጊቱን ከፈጸሙ በኋላ ፔርሲ ከፖሊሶች ለቀረበላቸው ጥያቄ "...በጣም አዝናለሁ፡፡ መነፅሬን ቤት በመርሳቴ ልሳሳት ችያለሁ" ሲሉ ቅሬታቸውን ገልጸዋል፡፡

(አዲስ ዘመን፣ የካቲት 10 ቀን 1975 ዓ.ም)

### ይድረስ ለ"ኮንዶም" ተጠቃሚዎች

በተለያዩ አገሮች ቀሳፊው በሽታ ማለትም ኤድስ እየተስፋፋ መምጣቱ ይታወቃል፡፡ ቢሆንም አንዳንድ ጠበብት እንደሚያስረዱት፤ ይሄንን ቀሳፊ በሽታ ለመከላከል ወንዶች "ኮንዶም" መጠቀም አለባቸው፡፡

ነገር ግን አንዳንድ ግለሰቦች የተጠቀሙበትን ኮንዶም የትም ስለሚጥሉት የነገ ሀገር ገንቢ የሆኑት ውድ ሕጻናት ይህን ኮንዶም በመጫወቻ መልክ እንደፊኛ በትንፋሻቸው በመንፋት ሲጫወቱ ተመልክቻለሁ፡፡ እውን ይህ ነገር በሕጻናቶች ላይ የጤና ችግር አይፈጥርምን?

ከተማሪ ደሳለኝ ተሾመ (ከፍቼ)

ከአዘጋጁ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚያትቱ በርካታ ደብዳቤዎች እየደረሱኝ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ፤ ከአሥመራ፤ ከናዝሬት፤ ከድሬዳዋ... ፡፡ ይኸው አሁን ደግሞ ከፍቼ!

ስለ ኮንዶም አንስቼ ዶክተር ጥበበ የማነ ብርሃንን አነጋግሬ ነበር፡፡ ስለ አጠቃቀሙ የነገሩኝን ለጊዜው ልተወው፡፡ ግለሰቦች ከተጠቀሙ በኋላ ግን በተቻለ መጠን ሕጻናት ከማያገኙበት ቦታ መጣል አለባቸው፡፡

(አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 15 ቀን 1994 ዓ.ም)

### ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

*አዳምና ሔዋን ገላቸውን በጨርቅ ያልሸፈኑት ለምንድነው?

አብደላ መሐመድ (ከናዝሬት)

-ያኔ ጨርቅ ስላልተፈጠረ ነው፡፡

*በአርሲ ጠቅላይ ግዛት ያሉት አንዳንድ ከበርቴዎች አዲስ ልብስ ሲገዙ በቅቤ ሳያጥቡ አይለብሱም ለምንድነው?

ዘካርያስ መንበሩ (ከጊቢ)

-በልማድ የመጣ የሀብታምነት መገለጫ ምልክት ነው፡፡

( አዲስ ዘመን፣ ጥር 20 ቀን 1969 ዓ.ም)

### "ስሜን ሰረቀ"

*የዛሬ ስድስት ዓመት የመሠረተ ትምህርት ፈተና ስፈትን ሸማኔው ሳምቢ "ጋሼ! ጋሼ!" እያለ ጣቱን ወደላይ ቀሰረ፡፡

ምንድነው ጋሼ ሳምቢ? ብለው፤ አጠገቡ ወደተቀመጠው ሰው ዞሮ "ይሄ ሰውዬ... ስሜን ሠረቀ" ብሎ በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በሙሉ አሳቀ፡፡

ሳምቢ አልተሳሳተም ነበር፤ አጠገቡ ያለው ጎልማሳ ሰው የፈተናው መልስ መስሎት የሳምቢን ስም አብሮ ኮርጆ ኑሯል፡፡

(አዲስ ዘመን፣ ጥር 4 ቀን 1982 ዓ.ም)

### ለፈገግታ

ሰውየው ጥንብዝ እያለ በመስከር ባለቤቱን ያሰለቸታል፡፡ ሚስት በዘመድ አዝማድ አስመክራ ስላልተሻለው ቢቸግራት ወደ ዶክተር ትሔድና "ዶክተር ባለቤቴ ሁል ጊዜ ማታ ማታ መጠጥ እየተጋተ ሙትት ብሎ እየገባ አስቸግሮኛል" ትለዋለች፡፡

ዶክተሩም ሙትት ብሎ ሲመጣ ጥሪኝ ብሎ ያሰናብታታል፡፡ ሰውየው እንደለመደው ምሽት ጠንብዞ በሸክም ይመጣና አልጋ ላይ ሲወድቅ ሚስት ስልክ ደውላ ሁኔታውን ለዶክተሩ ትነግራለች፡፡

ዶክተሩም ይመጡና ሲያዩት እውነትም ሕይወቱን የማያውቅ ሆኖ ያገኙታል፡፡ ወዲያው የሬሳ ሳጥን ያስመጡና ከነነፍሱ ተሸክመው በመክተት ይቆልፉበታል፡፡ እዚያው ከሳጥኑ ላይ አድሮ ንጋት ላይ ዶክተሩ ተመልሰው መጥተው ከሳጥኑ ውስጥ እንቅስቃሴ ሲጠባበቁ፤ ብንን ብሎ ቢወራጭ ሳጥኑ ሊያንቀሳቅሰው አልቻለም፡፡ በደንብ ሲያስብ በሬሳ ሳጥን መግባቱን ይገነዘባል፡፡ "ወይኔ ትላንትና ማታ ሞቻለሁ ማለት ነው" እያለ ከራሱ ጋር በማውራት ቀደም ብሎ የሞተውን ጓደኛውን ስም ያሰላስልና ጮክ ብሎ "ገብሬ ገብሬ" ሲል ዶክተሩ ወይ ይሉታል፡፡ እባክህ እኔም ትናንትና ማታ ሞቼ አንተ ወዳለህበት ስለመጣሁ እባክህን እዚህ አካባቢ መጠጥ ቤት ካለ ብታሳየኝ በማለት እየጮኸ ሲናገር "አዝናለሁ ባልሽ እንኳንስ በሕይወት እያለ ቢሞትም እንኳን መጠጥ ስለማይተው ልረዳሽ አልችልም" ብለው ዶክተሩ ወደቤታቸው ሔዱ፡፡

( አዲስ ዘመን፣ ኅዳር 13 ቀን 1989 ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ




## የሜክሲኮ አየር መንገድ ተሳፋሪ የአውሮፕላን በር ከፍቶ ክንፉ ላይ ተራመደ

በሜክሲኮ አንድ ተሳፋሪ የአደጋ ጊዜ መውጫ በርን ከፍቶ የአውሮፕላኑ ክንፍ ላይ ከተራመደ በኋላ በቁጥጥር ሥር ዋለ። ግለሰቡ የአደጋ ጊዜ መውጫ በር ከፍቶ የአውሮፕላኑ ክንፍ ላይ የተራመደው ከሜክሲኮ ወደ ጓቲማላ ሊበር የነበረው አውሮፕላን በቴክኒክ ችግር ለሰዓታት መዘግየት ካጋጠመው በኋላ ነው።


የሜክሲኮ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በክስተቱ ምክንያት በሰው ላይም ይሁን በአውሮፕላኑ ላይ የደረሰ ጉዳት አለመኖሩን አስታውቆ ግለሰቡ ለፖሊስ ተላልፎ ተሰጥቷል ብሏል። ይሁን እንጂ በኤሮሜክሲኮ አየር መንገድ አውሮፕላን ላይ ተሳፍረው የነበሩት ተሳፋሪዎች ድጋፋቸውን የአደጋ ጊዜ መውጫ በሩን ለከፈተው ግለሰብ ሰጥተዋል።

ተጓዦቹ መዘግየት ባጋጠመው አውሮፕላን ውስጥ ያለ አየር ማቀዝቀዣ እና ምግብ ለረዥም ሰዓት በአውሮፕላን ውስጥ እንዲቆዩ መደረጋቸው ለሕይወታቸው አደገኛ ሁኔታን ፈጥሮ እንደነበረ ገልጸዋል። ይህ ክስተት ያጋጠመው ባሳለፍነው ሐሙስ በአገሪቱ ሰዓት አቆጣጠር 11፡30 አካባቢ ላይ ነው። ከሜክሲኮ ሲቲ ወደ ጓቲማላ ሊበር የነበረው አውሮፕላን በጥገና ምክንያት መቀየር ስለነበረበት ተጓዦች ቢያንስ ለሦስት ሰዓታት ያክል በአውሮፕላን ውስጥ እንዲቆዩ ተደርገዋል።

በስም ያልተጠቀሰው የአደጋ ጊዜ መውጫ በሩን የከፈተው ግለሰብ ለፖሊስ ተላልፎ ተሰጥቷል ይባል እንጂ አሁንም በቁጥጥር ስር ውሎ ስለመገኘቱ አልያም ደግሞ ክስ ተመስርቶበት እንደሆነ ግልጽ አይደለም። በበረራው መዘግየት እጅግ ተበሳጭተው የነበሩት ተጓዦች ግን በሌላ አውሮፕላን ጉዟቸውን ቀጥለዋል።

ተሳፋሪዎቹ በማኅበራዊ ሚዲያ ባሰራጩት በእጅ የተጻፈ ጽሑፍ ግለሰቡ የአደጋ ጊዜ መውጫ በሩን የከፈተው "በሁሉም ሰው ድጋፍ ለሁሉም ተሳፋሪዎች ደኅንነት ሲባል ነው" ብለዋል። ተሳፋሪዎቹ ለሰዓታት በአውሮፕላኑ ውስጥ እንዲቆዩ በመደረጋቸው በአየር እጥረት "አደገኛ የጤና ሁኔታ" ተከስቶ ነበር ብለዋል።

"ሕይወታችንን ታድጓል" ሲሉ ተሳፋሪዎች ስም እና ፊርማቸው ያረፈበትን ጽሑፍ በስፋት በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ አሰራጭተዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



## የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋቾች በዳቢንቺ ሥዕል ሞናሊዛ ላይ ጉዳት ለማድረስ ሞከሩ

በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያለውን አያያዝ የሚቃወሙ ሁለት ሴቶች በፈረንሳይ ሙዚየም ውስጥ በሚገኘው የሊዎናርዶ ዳቪንቼ የሥዕል ሥራ በሆነችው ሞናሊዛ ላይ ሾርባ ደፍተዋል። ተቃዋሚዎቹ በመስታወት በተሸፈነው ስዕል ላይ የዱባ ሾርባ ከደፉ በኋላ ጤናማ እና ዘላቂ የምግብ አቅርቦት ይኑር የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተሳለችው እና በማዕከላዊ ፓሪስ በሚገኘው ዘ ሉቭ ሙዚየም የምትገኝ ሞናሊዛ በዓለም ላይ እጅግ እውቅ ከሆኑ የሥነ ጥበብ ሥራዎች መካከል አንዷ ናት። ክስተቱን ተከትሎ ሙዚየሙ በሰጠው መግለጫ የጥበብ ሥራው በጠንካራ መስታወት ስለተከለለ የደረሰ ጉዳት የለም ብሏል።

ሞናሊዛ ሥዕል ላይ ሾርባ የደፉት ሁለት ሴቶች፤ "ጠቃሚው የቱ ነው? ጥበብ ወይስ ጤና እና ዘላቂ የምግብ አቅርቦት?" ሲሉ ጠይቀዋል። ቀጥለው "የግብርና ሥርዓታችን ታሟል። ገበሬዎቻችን እየሞቱ ነው" ሲሉም ተደምጠዋል።'ሪፖስቴ አልሜንቴር' የተሰኘ ቡድን ለድርጊቱ ኃላፊነት እንደሚወስድ ገልጿል።

ቡድኑ በኤክስ ገጹ ባሰፈረው መልዕክት ሞናሊዛ ላይ ፈሳሽ መድፋት ያስፈለገው የምግብ አቅርቦት የማኅበራዊ ዋስትና አካል እንዲሆን የሚደረገው ጥረት ክፍል ነው ብሏል። ቀጥሎም አሁን ያለው የምግብ አቅርቦት ሥርዓት "መሠረታዊ የሆነውን የምግብ መብት" አያካትትም ሲል ወቅሷል። ቡድን ለዜጎች በየወሩ 150 ዩሮ የሚገመት የምግብ 'ኩፖን' እንዲሰጥ መጠየቁን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት

## የሠራተኛው ስፖርት “ለሰላም፣ ለጤናና ለምርታነማነት”

**ቦጋለ አበበ**

ለስድስት ወራት የሚካሄዱት የ2016 የበጋ ወራት ውድድሮች ሰላሳ የሚጠጉ የሠራተኛ ስፖርት ማሕበራትን በማሳተፍ ባለፈው እሁድ “የሠራተኛው ስፖርት ለሰላም፣ ለጤናና ለምርታማነት” በሚል መሪ ቃል በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ በደማቅ የመክፈቻ ስነስርዓት ተጀምሯዋል።

በኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ) አዘጋጅነት የቤት ውስጥ ውድድሮችን ጨምሮ በ10 የስፖርት አይነቶች ፉክክር በሚደረግበት የበጋ ወራት ውድድር በሁለቱም ፆታ በአትሌቲክስ፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ቮሊቮል፣ ዳማ፣ ቼስ፣ ገበጣ፣ ገመድ ጉተታና ሌሎችም የስፖርት አይነቶች ከ1ሺህ 500 በላይ ሠራተኞች ተሳታፊ ይሆናሉ።

በእግር ኳስና አትሌቲክስ፣ እንዲሁም በሌሎች አዝናኝ ውድድሮች በደመቀው የመክፈቻ ስነስርዓት ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢሠማኮ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አያሌው አሕመድ፣ የሠራተኞች ስፖርታዊ ተሳትፎ የሚሰሩበትን ተቋም ከማስተዋወቅና የቤተሰባዊ ባለድርሻነት ስሜትን ከማዳበር ባለፈ ጤናማ፣ ንቁና ምርታማ እንደሚያደርጋቸው ጠቅሰዋል።

“ስፖርታዊ ተሳትፎ ለማንኛውም የልማት ተቋም ቢሆን አትራፊ እንጂ አክሳሪ አይሆንም።” ያሉት አቶ አያሌው፣ ኢሠማኮ እስከ ዛሬም ድረስ ከራሱ ከሚመድበው በጀትና ቀና የስራ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም ባለሀብቶች በሚያደርጉለት የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በየዓመቱ የበጋና የክረምት ስፖርት ቻምፒዮናዎችን የሚያዘጋጀው አካላዊና ሕሊናዊ ብቃቱ የዳበረና ምርታማ ሠራተኛ ለማፍራት መሆኑን ተናግረዋል።

ኢሠማኮ አሰሪና ሠራተኞችን ለማግባባት፣ የልማት ተቋማትን ገፅታ ለመገንባትና የሠራተኞችን አንድነት ለማጠናከር ያለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ስለሚገነዘብም ውድድሮችን ለበርካታ ዓመታት እያከናወነ እንደሚገኝ ገልፀዋል።



**በእግር ኳስ የመክፈቻ ጨዋታ አዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ መከላከያ ኮንስትራክሽንን 2ለ1 አሸንፏል፣**

“ስፖርት አገራዊ አንድነትና ሰላምን ለማጠናከር እንዲሁም ዓለማቀፋዊ ቅርርቦሽን ለማስፈን ጭምር የሚያስችል ኃይል ያለው ‘ሰላማዊ’ መድረክ ነው” ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፣ እንዲህ አይነት ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ አካላዊ ደህንነትን ከማላቁ ባሻገር ለአእምሮና ለስሜት ደህንነት አስተዋፅኦው ቀላል እንዳልሆነ፣ ለስራው የበለጠ ተነሳሽነትና እርካታ ያለው የሰው ኃይል እንደሚፈጥርም አስረድተዋል።

አሰሪዎችም ይህን ለስፖርት የሚያውሉትን ሀብት እንደወጪ ብቻ ሳይሆን ለስራ ኃይላቸው ደህንነትና የእርስበርስ ቅርርብ መዋዕለ ንዋይ እንዳፈሰሱ ሊቆጥሩት ይገባል ብለዋል። ከእንዲህ አይነት ተነሳሽነቶች የሚገኙ ጥቅሞች ለአዎንታዊና ለበለፀገ የስራ ከባቢ አስተዋፅኦው ትልቅ መሆኑንም አክለዋል።

የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማሕበራት ኮንፌዴሬሽን ሕጋዊ እውቅና ካገኘበት ከሚያዝያ 01-1955 ዓ.ም ጀምሮ ሠራተኛው ከደመወዙ ላይ ለስፖርት አገልግሎት የሚውል የተለየ መዋጮ እንዲያዋጣ በማድረግና በጀት በመመደብ ለሠራተኞች አንድነት ማጠናከሪያና ለአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሻሻል ሲጠቀምበት ቆይቷል።

ከዚህ ጎን ለጎን ካለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት በላይ የሠራተኛው የስፖርት መድረክ ለአገራዊ ስፖርት እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ እያበረከተ መካሄዱን ቀጥሏል።

እነዚህ ውድድሮች ሠራተኞች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ፣ ጤናው የተጠበቀና አምራች ዜጋን ለማፍራት፣ የሠራተኞችን አንድነት ለማጠናከር፣ የልማት ተቋሞቻቸውን ማስተዋወቀና የባለቤትነት ስሜታቸው እንዲጠናከር ዓላማ በማድረግ የሚከናወኑ ናቸው። በኢትዮጵያ ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ አንጋፋ የስፖርት መድረኮች አንዱ የሆነው ይህ የሠራተኞች ውድድር በዚህ ዘመን ሠራተኛው በስፖርት የሚያደርገው ተሳትፎ ለሚሠራበት ድርጅት ውጤታማነት የሚኖረውን አስተዋጽኦ የጎላ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም ስፖርቱ የሠራተኛውን አንድነትና ለጋራ ጉዳይ አብሮ የመቆም ባሕሉን አጠናክሮበታል።

በአገሪቱ የተለያዩ ተቋማት ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞች በስፖርታዊ እንቅስቃሴ እየተሳተፉ ጤናማ፣ ንቁና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ውድድሮችን ማሰናዳት ውጤታማ ሠራተኛ ለማፍራት የሚያበረክቱት ሚናም ቀላል አይደለም።

በአሠሪና ሠራተኛው መካከልም ጥሩ ግንኙነት እንዲዳብር በማድረግ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ለኢንዱስትሪ ሰላም መስፈን የላቀ አስተዋጽኦ እንዳለውም ባለፉት በርካታ ዓመታት በተካሄዱ ውድድሮች ለመታዘብ ተችሏል።

በነዚህ ውድድሮች ላይ ተቋሞቻቸውን ወክለው በሚካፈሉ ተወዳዳሪዎች መካከል ከተቋም ጋር ያለውን መቀራረብ፣ ልምድ ማካፈል እንዲሁም ለተለያዩ ክለቦች ግብዓት የሚሆኑ ስፖርተኞች ማፍራት የቻለ ውድድር መሆኑንም በሠራተኛው ስፖርት ውስጥ ረጅም ዓመታትን ያሳለፉ ሰዎች ይመሰክራሉ። በውድድሩ በሚካፈሉ ተቋማት መካከል በሚፈጠረው ፉክክር ምክንያትም ሠራተኛው የተሻለ ውጤት ይዞ ለመምጣት ሲሽቀዳደምና ለዓመታዊ ውድድሩ ዝግጅት ሲያደርግ መመልከት የተለመደ መሆኑንም ያስረዳሉ።

የሰራተኛው የስፖርት መድረክ እንደ አገር በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ቢሆንም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እየተካሄደ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ከነዚህ ፈተናዎች አንዱ የተሳታፊ ማሕበራት ቁጥር በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉ ነው። የተሳታፊ ማሕበራትን ቁጥር ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ የኢሰማኮ የስፖርት ክፍል እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ ጥረት ማድረጉን እንደቀጠለ የሚናገሩት የኢሠማኮ የስፖርት ክፍል ኃላፊ አቶ ዮሴፍ ካሳ፣ “እኛ በርካታ ማሕበራት እንዲሳተፉ ጥያቄ እናቀርባለን የሚመጡት ግን በሚፈለገው ልክ አይደለም፣ ይህ ከበጀትና አሰሪዎች ለስፖርት ካላቸው አመለካከት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፣ ለስፖርቱ ግንዛቤና ጥሩ አመለካከት ያላቸው አሰሪዎች ሰራተኞችን የማሳተፉቸውን ያህል የሌላቸውም አሉ።” በማለት ምክንያቱን ያስረዳሉ።

አዳዲስ ማሕበራት ወደ ስፖርቱ የመምጣታቸውን ያህል በተለያዩ ምክንያቶች ነባር የነበሩ የሚቀሩበትም ሁኔታ አለ። አብዛኛው የእነዚህ ማሕበራት ችግር የበጀት ነው። ይሄ ሲስተካከል ግን ወደ ስፖርቱ ለመመለስ ፍላጎት አላቸው።

እንደ አቶ ዮሴፍ ገለፃ፣ የሰራተኛውን ስፖርት የሚያካሂድበት የራሱ የማዘውተሪያ ስፍራ አለመኖር ሁሌም የስፖርቱ ትልቅ ችግር ነው። ኢሰማኮ ሰራተኛው ስፖርታዊ ውድድሮቹን የሚያደርግበት የራሱ ማዘውተሪያ ስፍራ ባለቤት እንዲሆን ባለፉት ዓመታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ብዙ ጥረቶች ቢደረጉም አሁንም ችግሩ ሊቀረፍ አልቻለም።